ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 83ኛ ዓመት ቁጥር 055 ጥቅምት 25 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# ኢትዮጵያና ቼክ ሪፐብሊክ
## የኢኮኖሚ ትብብራቸውን ለማጠናከር ተስማሙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና ቼክ ሪፐብሊክ የኢኮኖሚ ትብብራቸውን ለማጠናከር ስምምነት አደረጉ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና የቼክ ሪፐብሊኩ ጠቅላይ ሚኒስትር ፔትር ፊያላ በጋራ ጉዳዮች ላይ ትናንት መወያየታቸውን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስታውቋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በማኅበራዊ የትስስር ገጻቸው፤ የቼክ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ፔትር ፊያላን በመቀበሌ ደስታ ተሰምቶኛል። ለጋራ ልማት እንዲበጀን በሀገሮቻችን መካከል በቆየው ግንኙነት ላይ ተመስርተን ግንኙነታችንን የበለጠ ማኅልበትን ዓላማ አድርገናል ብለዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ ውይይቱን አስመልክተው ትናንት በሰጡት መግለጫ፤ ሁለቱ ሀገራት ታሪካዊ ግንኙነት እንዳላቸው ተናግረዋል።

ሁለቱ ሀገራት በውትድርና፣ በኢንዱስትሪና በሌሎች

ኢትዮጵያና ቼክ ሪፐብሊክ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## በአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር የአየር ትንበያ አገልግሎት ማዕከል እየተገነባ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ወጪ በአፍሪካ ቀዳሚ የሆነ የአየር ትንበያ አገልግሎት ማዕከል እየገነባ መሆኑን የኢትዮጵያ ሜቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ሜቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢንስቲትዩቱ ሦስት ባለ ዘጠኝ ወለል የአየር ትንበያ ማዕከል ሕንፃዎችን እየገነባ ሲሆን ለግንባታውም አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ወጪ ይደረጋል፡፡

እየተገነቡ የሚገኙት ዘመናዊ ሕንፃዎች ዘመኑ ያፈራቸው የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችና በአርቴፊሻል ኢንተለጄንስ (AI) የበለጸጉ መሣሪያዎች የሚገጠምላቸው ሲሆን ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ የሳተላይት መረጃዎችን መጠቀም የሚያስችሉ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በአንድ ነጥብ ሦስት ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል

## «ጥቅምት 24፤ በየትኛውም ቦታ ሲደገም የማይገባውና ታሪክ የማይደረሳው አስከፊ ድርጊት ነው»

*- የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት*

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ጥቅምት 24፤ በየትኛውም ቦታ ሊደገም የማይገባውና ታሪክ የማይረሳው አስከፊ ድርጊት መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት «ጥቅምት 24፤ መቼም የትም አይደገምም» በሚል ርዕስ ትናንት በጽሑፍ በሰፈረው መግለጫ እንዳለው፤ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ለሀገሩ ክብር የሚከፍለው መስዋዕትነት በተግባር ከታየባቸው ቀናት መካከል ጥቅምት 24፣ 2013 ዓ.ም አንዱ ነው፡፡ በዕለቱ በመከላከያ ሠራዊት የሰሜን ዕዝ ላይ የደረሰው ጥቃት መቼም ቢሆን፣ በየትኛውም ቦታ ሊደገም የማይገባውና ታሪክ የማይረሳው አስከፊ ድርጊት ነው፡፡

በሠራዊታችን ላይ የተፈጸመው ጥቃት ሀገራችንን ከፍተኛ ዋጋ ያስከፈለ፣ ወደ አውዳሚ ጦርነት ጎትቶ ያስገባንና ከፍተኛ ሰብአዊና ቁሳዊ ኪሳራ ያደረሰ በመሆኑ ሊረሳ የማይችል፣ ሊደገም የማይገባው አሳፋሪና አሳዛኝ

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

የታሪክ አንጓ ነው ሲል መግለጫው አመልክቷል፡፡

ምንም እንኳን ጥቃቱን ተከትሎ የተገባበትን ጦርነት በሠላም ስምምነት መቋጨት ቢቻልም ቀኑ በታሪካችን እንደ ነውር

«ጥቅምት 24፤... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የአፈር አሲዳማነትን ለመከላከል ዘጠኝ ሚሊዮን ኩንታል ኖራ ለክልሉች ሊሰራጭ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የአፈር አሲዳማነትን ለመከላከል ዘጠኝ ሚሊዮን ኩንታል ኖራ ለክልሎች ለማሰራጨት ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። በዘንድሮ ዓመት 300 ሺህ ሄክታር መሬት በኖራ ለማከም ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን ገልጿል።

በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ የአፈር ሀብት ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሊሬ አብዩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት ዘጠኝ ሚሊዮን ኩንታል ኖራ ለክልሎች በማሰራጨት የአፈር አሲዳማነትን በቅንጅት ለመከላከል ጥረት ይደረጋል።

የግብርና ሚኒስቴር የአፈር አሲዳማነትን ለማከም ሰፊ ንቅናቄ እያካሄደ ነው ያሉት አቶ ሊሬ፤ በዘንድሮው ዓመት 300 ሺህ ሄክታር አሲዳማ መሬት በኖራ ለማከም ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

ክልሎች በጠየቁት ሄክታር መሠረት የተሰላ ዘጠኝ ሚሊዮን ኩንታል ኖራ መዘጋጀቱን ጠቁመው፤ የኖራ ምርቱ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በሲዳማ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች እንደሚሰራጭ

የአፈር አሲዳማነትን ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል


















ዜና

# ኢትዮጵያ ከ60 እስከ 80 በመቶ ድረስ የሳይበር ጥቃት ተጋላጭ ሀገር ናት

## -የሳይበር ጥቃትን ለመመከት ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ዝቅተኛው 60 በመቶ ከፍተኛው ደግሞ 80 በመቶ ድረስ የሳይበር ጥቃት ተጋላጭ ሀገር መሆኗን የኢንፎርሜሽ መረብ ደህንነት አስተዳደር ኤጀንሲ አስታወቀ።

ብሔራዊ የሳይበር ጥቃት ደህንነት በሚል በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ስር ባሉ ሦስት የሥራ ክፍሎች ላይ መሠረት ተደርጎ በተሠራ ጥናት እንደተገለጸው፤ የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት በኢትዮጵያ በጣም ከፍተኛ መሆኑ ተመልክቷል።

ጥናቱን ያቀረቡት የሳይበር ኦዲትና ኢቫሉሽን ዲቪዥን አክቲንግ አቶ ጥላሁን እጅጉ እንደገለጹት፤ ጥናቱ የተሠራው በሀገሪቱ ቁልፍ ተቋማትና ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት ቅርብ ይሆናሉ ተብለው በሚታሰቡ ተቋማት ላይ ነው። በጥናቱ መሠረትም ኢትዮጵያ ዝቅተኛው 60 በመቶ ከፍተኛው ደግሞ 80 በመቶ ድረስ የሳይበር ጥቃት ተጋላጭ ሀገር ናት።

አቶ ጥላሁን በ2015 ዓ.ም ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ ናቸው በተባሉ የመንግሥትና የግል 123 ተቋማት በመሠረተ ልማቶቻቸው፣ በሞባይል አፕሊኬሽናቸውና በድረ ገጾቻቸው ጥናት መደረጉን ጠቅሰው፤ በእነዚህ ተቋማት ላይ 187 የሚሆን ከፍተኛ አጋላጭ የሚያደርጓቸው ክፍተቶች መታየታቸውን ተናግረዋል።

ከእነዚህም ተቋማት በተሠራ የስጋት ዳሰሳም 82 በመቶ የሚሆኑት ተቋማት የሳይበር ደህንነት ላይ የሥራ መዋቅር የሌላቸው መሆናቸውን ገልጸው፤ 60 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ሳይበር ደህንነት ማስጠበቂያ



**አቶ ጥላሁን እጅጉ**

ቴክኖሎጂ የሌላቸው ናቸው ብለዋል።

ቴክኖሎጂው ኖሯቸው የሥራ መዋቅራቸው ዝቅተኛ ናቸው የተባሉት የሚዲያ ተቋማት ሲሆኑ ከፍተኛ መዋቅር ያላቸው ደግሞ የፋይናንስ ተቋማት መሆናቸውን ገልጸዋል።

በእነዚህ ተቋማት በተደረገው ዳሰሳም 75 በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይላቸው ወቅቱን የጠበቀ የሳይበር ደህንነት ምህዳሩን የተረዱ አለመሆናቸውን አብራርተዋል።

አቶ ጥላሁን የሳይበር ጥቃትን ለመመከት ክፍተት ያለባቸውን ተቋማት በመለየት ጥቃት ከመድረሱ በፊት ክፍተቶቹ እንዲሻሻሉ በማድረግና ሁሉም አካል የተቀናጀ ትብብር በማድረግ ተጋላጭነቱን መቀነስ ይቻላል ብለዋል።

አቶ ጥላሁን ኢትዮጵያ የምትገኝበት የጂኦ ፖለቲካ ሁኔታ ለሳይበር ጥቃት ዓይን ውስጥ እንድትገባ የሚያደርጋት መሆኑን ገልጸው፤ በ2013 በጀት ዓመት 2 ሺህ 898፣ በ2014 ደግሞ 8 ሺህ 845 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች መደረጋቸውን አውስተዋል።

የሚደረጉ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች ሀገሪቱ እንደምትገኝበት ፖለቲካዊ ሁኔታ የመጨመርና የመቀነስ አዝማሚያ ይኖረዋል ያሉት አቶ ጥላሁን፤ በ2015 በጀት ዓመት በሀገሪቱ አንጻራዊ ሠላም የተገኘ በመሆኑ ከ2014 በጀት ዓመት ጋር ከተደረጉ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች ጋር ሲነጻጸር ባለፈው ዓመት የተደረጉት የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች ወደ 6ሺህ 959 ዝቅ ማለታቸውን ገልጸዋል።

ከተደረጉ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎችም መሀከልም 2ሺህ 554 የሚሆኑት ጥቃቶች በተቋማት ዌብሳይት ላይ የተደረገ ሙከራ መሆኑን አመልክተው፤ አንድ ሺህ 493 ሙከራዎች ደግሞ የመሠረተ ልማቶችን ሲስተም ለማስተጓጎልና አገልግሎቶችን ለማቋረጥ የተደረጉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በሙከራዎቹ ኢላማ ተደርገው የነበሩ ተቋማት የፋይናንስ ተቋማት፣ የጸጥታና የደህንነት ተቋማት፣ የሚዲያ ተቋማት፣ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ ቴሌኮም፣ ጤና፣ ትምህርትና ሌሎች የመሠረተ ልማት ተቋማት ይገኙበታል።

የሳይበር ምህዳሩ መዘመን ተከትሎ ጊዜውን የሚመጥን የሰው ኃይል የቴክኖሎጂ ሁኔታ በሀገሪቱ የለም ያሉት አቶ ጥላሁን፤ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የሰው ኃይሉን መዘመንና ማብቃት እንደሚያስፈልግ መክረዋል።

# የንግድ ትርዒቱ የዘርፉን ተዋንያን በአንድ መድረክ ለማገናኘት ያግዛል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ የቆዳና የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ውጤቶች ለዕይታ የሚቀርቡበት የንግድ ትርዒት በዘርፉ የተሰማሩ ተዋንያንን በአንድ መድረክ ለማገናኘት እንደሚያግዝ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለጸ።

፱ኛው የአፍሪካ ሶርሲንግና የፋሽን ሳምንት አካል የሆነው የቆዳ፣ የጨርቃጨርቅ፣ አልባሳትና የፋሽን ኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ የንግድ ትርዒትና ኮንፍረንስ ትናንት በአዲስ አበባ ተጀምሯል።

በመክፈቻ መርሐ-ግብሩ ላይ የተገኙት የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል እንደተናገሩት፤ የንግድ ትርዒቱ በዘርፉ የተሰማሩ አቅራቢዎችና ሸማቾችን እንዲሁም ፖሊሲ አርቃቂዎችን በአንድ ስፍራ በማገናኘት ለዘርፉ ዕድገት በጎ አስተዋጽኦ ለማበርከት ያግዛል።

ከ50 በላይ ሀገራትን ከሚወክሉ ከ300 በላይ ላኪዎችን የሚያሳትፈው ዝግጅቱ የአፍሪካን የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪም ለማስተዋወቅ ይረዳል ብለዋል።

የንግድ ትርዒቱ የዘርፉን ምርቶችና ፈጠራዎችን



**አቶ መላኩ አለበል**

ለዓለም አቀፍ ታዳሚዎች ለማሳየት ሁነኛ መድረክ ሆኖ ያገለግላል ሲሉ አስረድተዋል።

በተዘጋጀው የንግድ ትርዒት ላይ በርካታ የአፍሪካዊ የአልባሳት አምራቾች፣ የተለያዩ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ተወካዮች፣ የቆዳ ውጤት አምራቾች፣ የቤት ውስጥ ማስጌጫዎች እና የፋሽን ዲዛይኖቻቸውን ለዕይታ እንዳቀረቡ አመላክተዋል።

የንግድ ትርዒቱ በመላው ዓለም የሚገኙ የዘርፉ ኢንቨስተሮችን የንግድ ሰዎችን በማሰባሰብ የተሻለ ሥራ ለማከናወን መነሻ እንደሚሆን ተናግረዋል።

መድረኩ የኢትዮጵያን የዘርፉን አቅም ለማሳየት ያግዛል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ከሌሎች አምራቾች ጋር ለመተባበርና የቴክኖሎጂ ዕውቀት ለመለዋወጥ እንደሚያግዝም አስረድተዋል።

የመንግሥት የረዥም ጊዜ ራዕይ ኢትዮጵያን በአምራች ኢንዱስትሪ በአፍሪካ ቀዳሚ ሀገር ለማድረግና መካከለኛ ገቢ ያለው ማኅበረሰብ መገንባት ነው ሲሉ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት የጨርቃጨርቅና ቆዳ ኢንዱስትሪዎች እሴት መጨመር፣ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት፣ የሥራ ዕድል መፍጠር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከል ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

የአፍሪካ ሶርሲንግና የፋሽን ሳምንት ዝግጅት ለጨርቃ ጨርቅ ምርቶችና ለተለያዩ የዘርፉ ግብዓት አቅራቢዎች የተዘጋጁ ማሽኖችን በማስተዋወቅ ረገድ ምቹ መድረክ ሆኖ ያገለግላል ብለዋል።

፱ኛው የአፍሪካ ሶርሲንግና ፋሽን ሳምንት ከጥቅምት 23 እስከ 26 ቀን 2016 ዓ.ም ይካሄዳል።



**አቶ ሲሬ ጀማል**

# የከተማዋን የውሃ ችግር የሚፈቱ ሦስት የውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታቸው 90 በመቶ ደርሷል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የከተማዋን የውሃ ችግር ለመፍታት በአንድ ቢሊዮን ብር በጀት እየተገነቡ ካሉት አምስት የውሃ ፕሮጀክቶች በተያዘው ዓመት ሦስቱ አገልግሎት ይሰጣሉ ሲል የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር አስታወቀ።

የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ሊሬ ጀማል በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አምስቱ ውሃ ፕሮጀክቶች ሲጀመሩ የከታማዋን ንጹህ የመጠጥ ውሃ ችግር ሙሉ በሙሉ ይፈታሉ ተብሎ ነው፡፡

ችግሩን ለመቅረፍ ከታለሙት አምስት ንጹህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ሦስቱ በመሠራት ላይ ሲሆኑ፤ እነዚህ ፕሮጀክቶች ዝርጋታቸው እየተጠናቀቀ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

እየተጠናቀቁ ያሉት ሦስቱ የንፁህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች እስካሁንም 530 ሚሊዮን ብር ወጪ ወጥቶባቸዋል ያሉት አቶ ሊሬ፤ ሦስቱ የውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታቸው በአማካኝ 90 በመቶ ደርሷል፡፡ ከሦስቱ አንዱ የውሃ ፕሮጀክት ኅዳር ወር 2016ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ሙሉ በሙሉ አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል ብለዋል፡፡

በኅዳር ወር አገልግሎት የሚሰጠው ውሃ ፕሮጀክት አንድ ቀበሌን መሸፈን የሚችል አቅም ያለው ሲሆን፤ በሰከንድ ሰባት ሊትር ውሃ ማመንጨት የሚችል ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡ ቀሪዎቹ ሁለት የንጹህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች አንድ ላይ 70 ሊትር በሰከንድ የሚያመነጩ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ሦስት የውሃ ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ የተቀሩት ሁለት ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታቸው ይጀመራል ያሉት ከንቲባው፤ አሁን ላይ የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራቸው ተጠናቋል ብለዋል፡፡

ሊጠናቀቁ የደረሱት ውሃ ፕሮጀክቶቹ አሁን በከተማዋ ያለውን የውሃ ችግር በጊዜያዊነት የሚቀርፉ መሆኑን አመልክተው፤ የሚያገኘውን ውሃ በተስተካከለና በቋሚነት እንዲያገኘው የሚያደርጉ ናቸው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ከተማዋ ግማሽ ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖርባት እንደመሆኗ በቂ የንጹህ ውሃ አቅርቦት ያስፈልጋል ያሉት ከንቲባው፤ የእነዚህ አምስት የውሃ ፕሮጀክቶች በከተማዋ ያሉትን ስድስቱንም ቀበሌዎች ይሸፍናሉ ብለዋል፡፡

የውሃ ፕሮጀክቶቹ ግንባታው የሚከናወነው በከተማ አስተዳደሩ በጀት ነው ያሉት አቶ ሊሬ፤ ሆኖም ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩና የማኅበረሰቡ ተሳትፎ ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የስታዲየሞቻችን ጉዳይ አፋጣኝ መፍትሔን ይሻል!

በመላው ዓለም ተወዳጅ የሆነው እግር ኳስ በዘመናችን ከስፖርትም የዘለለ ትርጉም አለው። በተለይም ከስፖርታዊ ውድድርና ከመዝናኛነት ባሻገር ምጣኔ ሀብታዊ እንድምታው እየጎላ መምጣቱ ለማንም ግልፅ ነው። ለዚህ አባባል በዓለም በዓመት በመቶ ቢሊዮን ዶላሮች የሚንቀሳቀስበት ግዙፍ ኢንዱስትሪ መሆኑ ጥሩ ማሳያ ነው።

ስፖርቱን በአግባቡ መጠቀም ለቻሉበት እንደ እንግሊዝ ዓይነት ሀገራት በዓመት ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ በማመንጨት ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ገቢን ከሚሸፍኑ ኢንዱስትሪዎች አራተኛ ደረጃ ላይ የሚቀመጥ ሆኗል።

በስፖርቱ ቀጥተኛ ተዋናይ የሆኑትን ተጫዋቾችና አሰልጣኞች ሳይጨምር በዓለም ደረጃ በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች የሥራ ዕድል እየፈጠረም ነው። በኢትዮጵያም ቢሆን እግር ኳስ በሺዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች እንጀራ ከመሆን አልፎ በዓመት በቢሊዮን የሚቆጠር ብር የሚንቀሳቀስበት ዘርፍ መሆኑ አያሻማም።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫ መሥራች ሀገር ናት፣ ከዚያም ባሻገር የአህጉሪቱን ትልቅ ውድድር ሦስት ጊዜ በማዘጋጀት አንድ ጊዜ ዋንጫ አንስታለች። ይድነቃቸው ተሰማን ዓይነት የተከበሩ የአፍሪካ እግር ኳስ ቁንጮ መሪዎችን ማፍራት የቻለች ሀገርም ናት።

ያም ሆኖ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ያለበት ደረጃ ራሱን የቻለ የሕዝብ ጥያቄ ቢሆንም ትልቅ የእግር ኳስ ፍላጎት ባለባት ሀገር የካፍና የፊፋን ዝቅተኛ መስፈርት የሚያሟላ አንድ ዓለም አቀፍ ጨዋታ የሚያስተናግድ ሜዳ ማጣቷ እንቆቅልሽ ሆኖ ዓመታት እየተቆጠሩ ነው።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ሰሞኑን 15ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ባካሄደበት ወቅት እንዳስታወቀው፤ በዓመቱ ለብሔራዊ ቡድን ከ106 ሚሊዮን ብር በላይ እያወጣ ነው፡፡ ደረጃውን የጠበቀ ስታዲየም ባለመኖሩም የወንዶች ብሔራዊ ቡድን በሌሎች ሀገራት ሜዳ ላይ እንዲጫወት ተገድዷል።

በዚህም ሀገሪቱ በዓመት ከ66 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ አድርጋለች። ፌዴሬሽኑም ብሔራዊ ቡድኑ በሀገሩ ባለመጫወቱ በአራት ዓመት 56 ሚሊዮን ብር የስፖንሰር ሺፕ ገቢ አጥቷል።

ብሔራዊ ቡድኑ በሜዳው ከማላዊ አቻው ጋር ያደርግ የነበረውን የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታ በሜዳ ችግር ምክንያት በሞዛምቢክ ማፑቶ እንዲያካሂድ በመወሰኑ፤ የሆቴል፣ የቡድን አባላቱ፣ የዳኞች የአውሮፕላን ወጪና አበልን ሳይጨምር፤ ለሜዳው ኪራይ ብቻ 8 ሺ ዶላር ለማውጣት ተገድዷል። ለአባላቱ የአውሮፕላን ጉዞም 1.9 ሚሊዮን ብር ወጪ አድርጓል።

አሁን ላይ የስታዲየሞችን ጉዳይ ከእግር ኳሳዊ ምክንያቶች ባለፈ ማየት የሚገባን ወቅት እንደሆነ ይታመናል። ብሔራዊ ቡድኑ ጨዋታዎችን በሜዳው ማድረግ ቢችል የተለያዩ ወጪዎቹን በብር ከመሸፈን ባለፈ፤ አሁን ላይ እንደ ሀገር ለውድድሮች ማስፈጸሚያ ወጪ የምናደርገውን የውጭ ምንዛሬ መታደግ ይቻላል። ሀገር ውስጥ ለሚካሄዱ ጨዋታዎች ከውጭ ሀገር የሚመጡ ቡድኖችና ደጋፊዎች ይዘው የሚመጡት የውጭ ምንዛሪ ተጠቃሚ መሆንም ቀላል ነገር አይደለም።

ከዚህም በላይ ብሔራዊ ቡድኑ በሜዳውና በደጋፊው የመጫወቱ ጉዳይ ቅንጦት ሳይሆን የክብር፣ የታሪክና የበርካታ ሕዝብ ፍላጎት ነው። ለቡድኑ ውጤታማነት ሊኖረው የሚችለው አሉታዊ አስተዋጽኦም፤ ለስፖርቱ ዕድገት የሚኖረው ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእግር ኳስ ስፖርት ካለው ፍቅር፤ በስፖርቱ በአህጉር ደረጃ ካለው ትልቅ ታሪክ አንጻር እንደ ሀገር አንድ ደረጃውን የጠበቀ ስታዲየም ባለቤት አለመሆናችን ሁሉንም ሊያስቆጭ የሚችል፤ ሀገራዊ ክብርን የሚያደበዝዝ፤ በስፖርቱ ላይ ጥላን የሚያጠላ ክስተት ነው።

ብሔራዊ ቡድኑ በሀገሩ መጫወት የሰፊው ሕዝብ ፍላጎት፣ የታሪክ፣ የሞራልና የገፅታ ግንባታ አንድ አካል ነው። ቢያንስ አንድ ዓለም አቀፍ መስፈርት የሚያሟላ ስታዲየም በተቻለ ፍጥነት ማዘጋጀት ለነገ የሚባል ሀገራዊ የቤት ሥራ ሊሆን አይገባም። በተለያዩ ክልሎች ግንባታቸው ተጀምሮ ያልተጠናቀቁ ስታዲየሞችን አቅም ታሳቢ ባደረገ መንገድ ማጠናቀቅ የሚቻልበትን አግባብ መፍጠርም ተገቢ ነው።

ለዚህ ደግሞ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፣ ስታዲየሞቹ የሚገኙባቸው ክልሎች፣ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽንና ባለሀብቶች በአጠቃላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንደ ተቋም እና ዜጋ የሚጠበቅባቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከት ከፍባለ ቁጭት እና ቁርጠኝነት እየተናበቡ ሊንቀሳቀሱ ይገባል።


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70



በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service


## ጥቅምት 24፤

### መቼም የትም አይደገምም!

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ለሀገሩ ክብር የሚከፍለው መስዋዕትነት በተግባር ከታየባቸው ቀናት መካከል ጥቅምት 24፣ 2013 ዓ.ም አንዱ ነው። በዕለቱ በመከላከያ ሠራዊት የሰሜን ዕዝ ላይ የደረሰው ጥቃት በሀገራችን ታሪክ ጥቁር ጠባሳ አሳርፎ ያለፈ ክስተት ነው። ይህ በሠራዊቱ አባላት ላይ የተፈጸመው ጥቃት መቼም ቢሆን፣ በየትኛውም ቦታ ሊደገም የማይገባውና ታሪክ የማይረሳው አስከፊ ድርጊት ነው።

በሠራዊታችን ላይ የተፈጸመው ጥቃት ሀገራችንን ከፍተኛ ዋጋ ያስከፈለ፣ ወደ አውዳሚ ጦርነት ጎትቶ ያስገባንና ከፍተኛ ሰብአዊና ቁሳዊ ኪሳራ ያደረሰ በመሆኑ ሊረሳ የማይችልና ሊደገም የማይገባው አሳፋሪና አሳዛኝ የታሪክ አንጓ ነው። ምንም እንኳን ጥቃቱን ተከትሎ የተገባበትን ጦርነት በሠላም ስምምነት መቋጨት ቢቻልም ቀኑ በታሪካችን እንደ ነውር መቆጠር ያለበት ተግባር የተፈፀመበት ቀንና ትምህርት የሚወሰድበት ክስተት በመሆኑ ዕለቱ ሁሌም ሊዘከር ይገባል።

ይሄንን ቀን የምናስበው ለቂምና ለበቀል አይደለም። ያ ስህተት እንዳይደገም ነው። እናቶች የሚያለቅሱበት፤ ወጣቶች የሚማገዱበት፣ የሕዝቦች ትሥሥር የሚላላበት፤ ቤተሰብ የሚበተንበት፣ የሀገር ሀብት የሚወድምበት የጦርነት መንገድ ይብቃ ለማለት ነው።

ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የተፈጸመውን ጥቃት በመቀልበስ በኢትዮጵያ ላይ ተከፍቶ የነበረውን ጦርነት በጋራ ርብርብ መክተን የሀገራችንን የግዛት አንድነት እና ሉዓላዊነት አስጠብቀናል። ይህም ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚደረግ ማንኛውም ጥረት ሊሳካ እንደማይችል ፅኑ ማሳያ ነው፡፡ በመሣሪያ ኃይል ሥልጣን ለመቆጣጠር የሚደረግ ጥረት በኢትዮጵያ ምድር ሊሳካ እንደማይችል አረጋግጧል።

> **መ**ንግሥት ለዘላቂ ሀገራዊ ሠላምና ለሀገር አንድነት ሲል ችግሩን በሠላማዊ መንገድ ለመቋጨት የወሰነው፤ ተመሳሳይ ስህተቶች በየትኛውም አካባቢና ጊዜ እንዳይደገሙ ትምህርት እንዲወሰድበት ለማስቻል ነው። መከላከያ ሠራዊትን ማጥቃት መደገም የሌለበት ትልቅ ስህተት መሆኑን በዚህ ወቅት በየጥሻው የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎች ሊገነዘቡት ይገባል

መንግሥት ለዘላቂ ሀገራዊ ሠላምና ለሀገር አንድነት ሲል ችግሩን በሠላማዊ መንገድ ለመቋጨት የወሰነው፤ ተመሳሳይ ስህተቶች በየትኛውም አካባቢና ጊዜ እንዳይደገሙ ትምህርት እንዲወሰድበት ለማስቻል ነው። መከላከያ ሠራዊትን ማጥቃት መደገም የሌለበት ትልቅ ስህተት መሆኑን በዚህ ወቅት በየጥሻው የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎች ሊገነዘቡት ይገባል።

መከላከያ ሠራዊታችንን ማጥቃት የሀገራችን የኀልውናዋ የመጨረሻ ምሽግን መንካት እንደሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል። በየመንደሩ እየዞሩ የሕዝብን ሠላም የሚነሱ፣ ዝርፊያ የሚፈጽሙና ሀብት የሚያወድሙ አካላትም እየሄዱበት ያለው መንገድ የስህተት መሆኑን ተገንዝበው መከላከያ ሠራዊታችን ላይ የሚፈፅሙትን ትንኮሳ ሊያቆሙ ይገባል። ወንዝ የማያሻግር የፅንፈኝነት ዓላማ አንግበው የሚንቀሳቀሱ የመንደር ታጣቂዎች፤ ትልቅ ሀገራዊ ራዕይ ሰንቆ የተሰለፈውን መከላከያ ሠራዊታችንን በማጥቃት ምንም ዓይነት ድል እንደማያገኙ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ዘብ የቆመው ሠራዊታችን ዛሬም በተግባር እያረጋገጠ ይገኛል።

መከላከያ ሠራዊታችን በጥቅምት 24 የደረሰበትን ጥቃት አልፎ፣ ሀገራችን ላይ የተከፈተውን ጦርነት መክቶና የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት በመሥዋዕትነቱ አስከብሮ ኢትዮጵያን ከታላቅ አደጋ ታድጓል። በዚህ ወቅት መከላከያ ሠራዊቱ ለሀገራችን እየከፈለ ያለውን ክቡር መሥዋዕትነት በማቃለል የሐሰት ቅስቀሳ የሚያሰራጩ አካላትም ከባለፈው ስህተት ተምረው ከእኩይ ተግባራቸው ሊታቀቡ ይገባል።

ጥቅምት 24 ጥቃት የተፈጸመበት ጀግናው ሠራዊታችን አሁን ላይ የበለጠ ዐቅሙን በሰው ኃይል፣ በሥነምግባር፣ በመሣሪያ፣ በቴክኖሎጂና በወታደራዊ ሳይንስ ገንብቶ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከማንኛውም የውስጥም ሆነ የውጭ ጥቃት ጠብቆ ኢትዮጵያን ወደላቀ ከፍታ ለማሸጋገር በሚችልበት አስተማማኝ ቁመና ላይ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ምንጊዜም ፍላጎታቸው ሠላም፣ ልማትና አብሮነት ብቻ ነው። የሀገር መከላከያ ሠራዊታችንም እነዚህን የሕዝብና የመንግሥት ፍላጎቶች እውን ለማድረግ ማንኛውንም መሥዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ነው፤ እየከፈለም ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ቅጥረኞች የሀገር መከላከያ ሠራዊት ላይ የሐሰት ዘመቻዎችን ከፍተው የሠራዊቱን ክቡር ስም ለማጠልሸት ሲሞክሩ ታይቷል። ሆኖም ሠራዊታችን እንኳን ከሃሰተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ በጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በተፈጸመበት ጥፋት እንኳ የማይንበረከክ ፅኑ መሠረትና ኢትዮጵያዊ ጀግንነት የተላበሰ መሆኑን ወዳጅም ጠላትም ያውቀዋል።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም በተለመደው ደጀንነቱ ሠራዊቱን ለላቀ ድልና ክብር እያበረታታ ይገኛል። ይህንን ተግባሩንም አጠናክሮ ሊቀጥልበት ይገባል። መከላከያ ሠራዊትን የማጥቃት የባንዳነት ተግባር በማንኛውም ወቅትና ሁኔታ ሊወገዝ የሚገባው ተግባር ነው። ለዚያም ነው ዘንድሮ የጥቅምት 24ን ለሦስተኛ ዓመት ስናስብ ይህ ዓይነት የሀገር ክህደት እንዳይረሳም እንዳይደገምም የምንዘክረው።

**ክብር ለሀገር ሉዓላዊነት ለተሠዉ ጀግኖች!!**

**ይቅር እንላለን ግን አንረሳም።**

ዜና

# «ጥቅምት 24፤ በየትኛውም ቦታ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መቆጠር ያለበት ተግባር የተፈፀመበት ቀንና ትምህርት የሚወሰድበት ክስተት በመሆኑ ዕለቱ ሁሌም ሊዘከር እንደሚገባ አገልግሎቱ አስታውቋል፡፡

እንደ መንግሥት ኮሙኒኬሽን መግለጫ፤ ይሄንን ቀን የምናስበው ለቂምና ለበቀል አይደለም። ያ ስህተት እንዳይደገም ነው። እናቶች የሚያለቅሱበት፤ ወጣቶች የሚማገዱበት፣ የሕዝቦች ትሥሥር የሚላላበት፤ ቤተሰብ የሚበተንበት፣ የሀገር ሀብት የሚወድምበት የጦርነት መንገድ ይብቃ ለማለት ነው።

ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የተፈጸመውን ጥቃት በመቀልበስ በኢትዮጵያ ላይ ተከፍቶ የነበረውን ጦርነት በጋራ ርብርብ መክተን የሀገራችንን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት አስጠብቀናል ያለው መግለጫው፤ ይህም ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚደረግ ማንኛውም ጥረት ሊሳካ እንደማይችል ፅኑ ማሳያ ነው። በመሣሪያ ኃይል ሥልጣን ለመቆጣጠር የሚደረግ ጥረት በኢትዮጵያ ምድር ሊሳካ እንደማይችል አረጋግጧል ብሏል፡፡

መንግሥት ለዘላቂ ሀገራዊ ሠላምና ለሀገር አንድነት ሲል ችግሩን በሠላማዊ መንገድ ለመቋጨት የወሰነው፤ ተመሳሳይ ስህተቶች በየትኛውም አካባቢና ጊዜ እንዳይደገሙ ትምህርት እንዲወሰድበት ለማስቻል መሆኑን መግለጫው አመልክቶ፤ መከላከያ ሠራዊት ማጥቃት መደገም የሌለበት ትልቅ ስህተት መሆኑን በዚህ ወቅት በየጥሻው የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎች ሊገነዘቡት ይገባል ሲል ገልጿል፡፡

መከላከያ ሠራዊታችንን ማጥቃት የሀገራችን የኀልውናዋ የመጨረሻ ምሽግን መንካት እንደሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ በየመንደሩ እየዞሩ የሕዝብን ሠላም የሚነሱ፣ ዝርፊያ የሚፈጽሙና ሀብት የሚያወድሙ አካላትም እየሄዱበት ያለው መንገድ የስህተት መሆኑን ተገንዝበው መከላከያ ሠራዊታችን ላይ የሚፈፅሙትን ትንኮሳ ሊያቆሙ ይገባል ሲል አስገንዝቧል፡፡

ወንዝ የማያሻግር የፅፈኝነት ዓላማ አንግበው የሚንቀሳቀሱ የመንደር ታጣቂዎች፤ ትልቅ ሀገራዊ ራእይ ሰንቆ የተሰለፈውን መከላከያ ሠራዊታችንን በማጥቃት ምንም ዓይነት ድል እንደማያገኙ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ዘብ የቆመው ሠራዊታችን ዛሬም በተግባር እያረጋገጠ ይገኛል ሲል ነው መግለጫው ያብራራው፡፡

መከላከያ ሠራዊታችን በጥቅምት 24 የደረሰበትን ጥቃት አልፎ፣ ሀገራችን ላይ የተከፈተውን ጦርነት መክቶና የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት በመሥዋዕትነቱ አስከብሮ ኢትዮጵያን ከታላቅ አደጋ ታድጓል ያለው መግለጫው፤ በዚህ ወቅት መከላከያ ሠራዊቱ ለሀገራችን እየከፈለ ያለውን ክቡር መሥዋዕትነት በማቃለል የሐሰት ቅስቀሳ የሚያሰራጩ አካላትም ከባለፈው ስህተት ተምረው ከእኩይ ተግባራቸው ሊታቀቡ እንደሚገባ አሳስቧል፡፡

ጥቅምት 24 ጥቃት የተፈጸመበት ጀግናው ሠራዊታችን አሁን ላይ የበለጠ ዐቅሙን በሰው ኃይል፣ በሥነምግባር፣ በመሣሪያ፣ በቴክኖሎጂና በወታደራዊ ሳይንስ ገንብቶ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ከማንኛውም የውስጥም ሆነ የውጭ ጥቃት ጠብቆ ኢትዮጵያን ወደላቀ ከፍታ ለማሸጋገር በሚችልበት አስተማማኝ ቁመና ላይ እንደሚገኝም የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መግለጫ አመልክቷል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ምንጊዜም ፍላጎታቸው ሠላም፣ ልማትና አብሮነት ብቻ መሆኑን ገልጾ፤ የሀገር መከላከያ ሠራዊታችንም እነዚህን የሕዝብና የመንግሥት ፍላጎቶች እውን ለማድረግ ማንኛውንም መሥዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ነው፤ እየከፈለም መሆኑን አንስቷል፡፡

ይሁን እንጂ አንዳንድ ቅጥረኞች የሀገር መከላከያ ሠራዊት ላይ የሐሰት ዘመቻዎችን ከፍተው የሠራዊቱን ክቡር ስም ለማጠልሸት ሲሞክሩ ታይቷል ያለው መግለጫው፤ ሆኖም ሠራዊታችን እንኳን ከሃሰተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ በጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በተፈጸመበት ጥፋት እንኳ የማይንበረከክ ፅኑ መሠረትና ኢትዮጵያዊ ጀግንነት የተላበሰ መሆኑን ወዳጅም ጠላትም ያውቀዋል ሲል አስታውቋል፡፡

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም በተለመደው ደጀንነቱ ሠራዊቱን ለላቀ ድልና ክብር እያበረታታ ይገኛል። ይህንን ተግባሩንም አጠናክሮ ሊቀጥልበት እንደሚገባ አመልክቶ፤ መከላከያ ሠራዊትን የማጥቃት የባንዳነት ተግባር በማንኛውም ወቅትና ሁኔታ ሊወገዝ የሚገባው ተግባር ነው፡፡ ለዚያም ነው ዘንድሮ የጥቅምት 24ን ለሦስተኛ ዓመት ስናስብ ይህ ዓይነት የሀገር ክህደት እንዳይረሳም እንዳይደገምም የምንዘክረው ብሏል፡፡

# ኢትዮጵያና ቼክ ሪፐብሊክ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የኢኮኖሚ ዘርፎች የቆየ የትብብር ግንኙነት እንዳላቸው አስታውሰው፤ አዳዲስ የኢኮኖሚ ትብብሮች ማጠናከር በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ውይይት መደረጉን አንስተዋል።

በተለይ በሁለቱ ሀገራት መካከል በግብርና ኢንቨስትመንት፣ በውትድርና ቴክኖሎጂ ዘርፍ፣ በመሠረተ ልማት ዘርፎች በጋራ መሥራት የሚቻልባቸውን መንገዶች ለማመቻቸት ዓላማ ያደረገ ስምምነት መደረጉን አስረድተዋል።

ከቼክ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር በርካታ የቢዝነስ ልዑካን ቡድን አባላት ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል ያሉት አምባሳደር ምስጋኑ፤ በኢኮኖሚ ዘርፍ ያለውን አጋርነት አጠናክሮ መቀጠል የሚያስችል ዕድል መፈጠሩን ጠቁመዋል።

ሀገራቱ በውሃ፣ በጤናና በተለያዩ ዘርፎች ያላቸውን ትብብር መሠረት ያደረገ ጉብኝት እንደተደረገም አስረድተዋል።

በኢትዮጵያ የቼክ ሪፐብሊክ አምባሳደር ሚሮስላቭ ኮሴክ በበኩላቸው፤ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት ለበርካታ ዓመታት የዘለቀ መሆኑን አንስተዋል።

የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት በበርካታ የትብብር መስኮች ላይ መሠረት ያደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ ሀገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ያላት የልማት ትብብር ጠንካራ ነው ብለዋል።

ይህንንም ተከትሎ በኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ ልማትና ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ለማስቀጠል መንግሥት የሚያደርገውን ጥረት ቼክ እየደገፈች መሆኑንም ገልጸዋል።

ግብርና፣ የአየር ንብረት ለውጥ መከላከልና ማዕድን በሀገራቱ መካከል ያሉ ተጠቃሽ የትብብር መስኮች መሆናቸውን አስረድተዋል።

ሀገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር በንግድና ኢንቨስትመንት ለመተሳሰር ጽኑ ፍላጎት እንዳላት አመልክተው፤ በጤና፣ በትምህርት፣ በባህል ልውውጥ ዘርፎች አጋርነታቸውን ለማጠናከር እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ቼክ ሪፐብሊክ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የኢኮኖሚ ትስስር ለማጠናከርም በቅርቡ ከሁለቱም ሀገራት የተውጣጡ የባለድርሻ አካላት የቢዝነስ ፎረም እንደሚካሄድ አምባሳደሩ ገልጸዋል።

ለሁለት ቀናት ይፋዊ ጉብኝት ቆይታ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ፔትር ፊያላና ልዑካቸው የውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴርን ጎብኝተዋል።

የውኃና ኢነርጂ ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋን (ዶ/ር) ጨምሮ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

ኢትዮጵያና ቼክ ሪፐብሊክ የከርሰ ምድርን ውኃ በምርምር ጥቅም ላይ ማዋል (ሃይድሮጂኦሎጂ) ዙሪያ ለረጅም ጊዜ የቆየ ትብብር ያላቸው መሆኑ ተጠቁሟል።

# ነፃ ሃሳብ



በቀምሳቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፣ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፣ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፣ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## መኅልዬ መኅልዬ ዘ ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጄታ፤

መኅልዬ መኅልዬ ዘሰሎሞን ከሁሉም የሚበልጥ የሰለሞን መዝሙር ማለት ነው:: የሁለት ፍቅረኛሞች ንግግር ተደርጎም ይወሰዳል:: የፍቅረኞች ንግግር በግጥም ነውና ምት፣ ዜማ አለው:: ሰለሞን ስለ ሙሽራውና ሙሽሪት፣ ስለፈጣሪና ስለ ቤተ ክርስቲያን የዘመራቸውን 1005 መዝሙሮችን ይመለከታል:: ሙሽራው ልዑል እግዚአብሔርን ሲወክል ሙሽራይቱ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት:: መኅልይ ለዘብ ያለ ወረብ አይነት በፍጥነት የሚዘመር ጥዑም ዜማ ነው ::

መዝሙሮቹ በተለያየ ስልት ዜማ ቢደጋገሙም ያው ስለፈጣሪና ቤተ ክርስቲያን ክብር፣ ቅድስና የሚመስክሩ ናቸው:: ይህ መጣጥፍ ታላቁን “የማሽላውን አባት” የሚዘክር፣ የሚያወድስና የሚያከበር ሆኖ ስለአገኘሁት “መኅልየ መኅልይ ዘ ፕሮፌሰር ገቢሳ እጄታ” ማለትን መርጫለሁ ::

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ብሔራዊ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ፈጠራ ዘርፍ ሜዳልያ በዋይት ሐውስ ካበረከቱላቸው አንዱ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጄታ ናቸው። ሽልማቱ የተሰጠው ባጠቃላይ ለ21 አሜሪካውያን ተመራማሪዎች ነው። ሽልማቱ በሳይንስ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ላበረከቱ የሚሰጥ ነው ይለናል የእንግሊዙ ዜና ማሰራጫ ቢቢሲ።

ከዘንድሮው ተሸላሚዎች መካከል አነስተኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት ንጹሕ የመጠጥ ውሃ በማቅረብ እንዲሁም በረሃን የሚቋቋሙ ዕፅዋት በማብቀል የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ እንደሆኑ ፕሬዚዳንት ባይደን በሥነ ሥርዓቱ ላይ ተናግረዋል። “የሰው ልጆችን አኗኗር የሚያሻሽሉ ግኝቶች ናቸው። እንደ ካንሰርና ፓርኪንሰንስ ያሉ ሕመሞችን ለማከም አስተዋፅዖ ያበረከቱም ይገኙበታል” ብለዋል።

ኢትዮጵያዊ አሜሪካዊው ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ የተሸለሙት በዕፅዋት ዘረ መል ምሕንድስና ሲሆን፣ የበረሃን የአየር ንብረት የሚቋቋሙ ዝርያዎች በማግኘታቸው ሽልማቱ ተበርክቶላቸዋል። ይህ ግኝት የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጥ ነው። ፕሮፌሰር ገቢሳ በአሜሪካ ኢንዲያና በሚገኘው ፕሪዲዩ ዩኒቨርስቲ ተመራማሪ ናቸው። በዩኒቨርስቲው የዓለም አቀፍ ምግብ ዋስትና ክፍል ዋና ዳይሬክተር ሲሆኑ፤ በዕጽዋት ማርባት፣ በዕፅዋት ዘረ መል እንዲሁም ዓለም አቀፍ ግብርና አንቱታን ያተረፉ ጉምቱ ሊቅ ናቸው።

ተሸላሚዎቹ በግኝታቸው ለሳይንሳዊ እመርታ ፈር ቀዳጆች እንደሆኑ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን በዋይት ሐውስ ንግግራቸው ጠቅሰዋል። “ሁላችሁም ተሸላሚዎች ስለ ጀግንነታችሁ እናመሰግናለን”። ከተሸላሚዎቹ መካከል ከተለያዩ አገራት አሜሪካ የሄዱ ሳይንቲስቶች እንደሚገኙበት በመጥቀስም “አሜሪካ የሚገልጻት አንድ ቃል ቢኖር ዕድሎች ነው” ብለዋል ፕሬዚዳንቱ። ከዚህ ዕድል ተቋዳሽ ከሆኑት ሳይንቲስቶች መካከል አንዱ ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጄታ ናቸው። ተወልደው ያደጉት ኢትዮጵያ ነው። በዓለም በዘረ መል ምርምር አሉ ከሚባሉ ባለሙያዎች ግንባር ተጠቃሽ ናቸው። ከዚህ ቀደም የዓለም ምግብ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። በዋናነት ምርምር የሚያደርጉት በማሽላ ላይ ነው።

አሜሪካ በሳይንስ ዘርፍ የመሪነት ሚና እንደምትጫወት፤ ተሸላሚዎቹ የዚህ አካል እንደሆኑም በንግግራቸው ጠቅሰዋል። “እዚህ የተገኛችሁት ተሸላሚዎች አሜሪካውያን ውጤት ሳይገኝ የሚረቱ ወይም ጥረት የሚያቆሙ እንዳልሆኑ ማሳያ ናችሁ” ብለዋል። ፕሮፌሰር ገቢሳ የዕፅዋት ዘረ መል፣ የዘረ መል ለውጥና ዘር ሐረግ በሚያጠናው ዘርፍ (Plant Genetics) ነው ምርምር የሚያደርጉት። ሽልማቱ የተበረከተላቸው ድርቅ መቋቋም የሚችል የማሽላ ዝርያ በማዋቀር ነው። “ለሚሊዮኖች የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጥ ግኝት ነው” በሚል በሽልማት ሥነ ሥርዓቱ ላይ ተገልጿል።

> “ኢንተርኔት በማይገኝበት ሁኔታ ውስጥ ምን እየተካሄደ እንዳለ ማወቅ አይቻልም፤ መልዕክቱም ከማላውቀው ሰው ስለሆነ የደረሰኝ ማረጋገጥ ነበረብኝ። አሁን ባለንበት ሁኔታም እንደዚህ አይነት ነገር ስለማልጠብቅ ሽልማቱ አስደንቆኛል”

በሳይንስና ፖሊሲ ዘርፍ እንዲሁም በምጣኔ ሀብት ማሻሻል ረገድ ፕሮፌሰር ገቢሳ ያበረከቱት አስተዋፅዖ ለአርሶ አደሮች የተሻለ ሁኔታ መፍጠር የቻለ እንደሆነ ተገልጿል። “ሀገራትን የሚያጠናክርም ነው” በማለት ስለ ምርምራቸው በዋይት ሐውሱ የሽልማት ሥነ ሥርዓት ተገልጿል። እአአ በ2009 ‘ወርልድ ፉድ ፕራይዝ’ የተሸለሙት ማሽላን በማዳቀል ድርቅ እና አረም የሚቋቋም ለማድረግ ባደረጉት ምርምር ነበር። ይህ ጥናታቸው ከሰሐራ በታች ባሉ ሀገራት በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን ለመመገብ ማስቻሉን ፕሪዲዩ ዩኒቨርስቲ በድረ ገጹ ላይ አስፍሯል።

ፕሮፌሰር ገቢሳ“ውጤት መር ምርምር በማድረግ ነው የሚታወቁት። በታዳጊ አገራት ከ500 ሚሊዮን በላይ ሰዎችን የሚመግበውን ማሽላ ድርቅ የሚቋቋም ማድረግ ችለዋል” ይላል ድረ ገጹ። ማሽላ በምርት ወቅት ሊገጥመው የሚችለውን ችግር በመፍታት የተመጣጠነ ይዘት እንዲኖረው እንዲሁም ድርቅና ቅዝቃዜንም እንዲችል በማድረግ ምርምራቸው ይታወቃሉ። ማሽላው ከአረም በተጨማሪ የዕፅዋት ሕመምን መቋቋም የሚችልም ነው። ዘረ መላቸው የተሻሻለ የማሽላ ዓይነቶችን በአሜሪካ እንዲሁም በአፍሪካ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተመራማሪው አስችለዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን በአሜሪካ የመንግሥት ተቋማትን በሳይንስና ፖሊሲ በማማከር አገልግለዋል። የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ እአአ በ2010 የአፍሪካ የሳይንስ ልዑክ አድርገው ሾመዋቸው ነበር። በ2013 በቀድሞው የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ባንኪ ሙን የሳይንስ አማካሪ ቦርድ ሆነው ተሹመው ነበር። ከሮኬፌለር ፋውንዴሽን፣ ከፋኦ እና ሌሎችም ተቋማት ዕውቅና ተሰጥቷቸዋል።

የዓለም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሠሩት ሥራ በዓለም መድረክ ስማቸውንና የሀገራቸውን ስም ያስጠሩ ፀሐፊ፣ አርታኢ፣ መምህር፣ አማካሪ እና ተመራማሪ የዓለም ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታን ከረዥሙ የሕይወት ጉዞአቸው በጥቂቱ ይዘንላችሁ ቀርበናል ይለናል አዲስ ማለዳ:: ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ ከአዲስ አበባ 62 ኪሎሜትር በስተምዕራብ ርቀት ላይ በምትገኘው አሎንኮሜ በምትባል መንደር በ1950 እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ተወለዱ:: የቄስ ትምህርታቸውን በአካባቢያቸው ሲከታተሉ ቆይተው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በአካባቢያቸው ስላልነበረ 20 ኪሎሜትር በእግራቸው ተጉዘው ተከታትለዋል::

የዓለም ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በጅማ የግብርና ቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጅ የተከታተሉ ሲሆን፤ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በዕፅዋት ሳይንስ ከዓለማያ ኮሌጅ በ1973 ዓ.ም ወስደዋል:: እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1976 በዕፅዋት ሳይንስ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንዲሁም በ1978 በዕፅዋት ማዳቀል እና ዘረመል ኢንጂነሪንግ አሜሪካ ከሚገኘው ፔድሩ ዩኒቨርስቲ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል::

ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ ከሁለት መቶ በላይ የጥናት ጽሑፎችን ለኅትመት ያበቁ ሲሆን፤ አራት መጽሐፎችን የአርትዖት ሥራ ሠርተዋል:: ላለፉት 28 ዓመታት በአሜሪካ በሚገኘው ፔድሩ ዩኒቨርስቲ ያገለገሉት የዓለም ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ ዩኒቨርሲቲው አሉኝ ከሚላቸው ተመራማሪዎችም አንዱ ናቸው:: ዶክትሬታቸውን ከተመረቁ በኋላ ወደ ሱዳን በመሄድ ማሽላ ላይ ምርምራቸውን ቀጥለዋል:: በምርምራቸውም ድርቅን መቋቋም የሚችል የማሽላ ዝርያ ለዓለም ማኅበረሰብ ማበርከት ችለዋል::

በ150 እጥፍ ምርታማነትን የሚጨምር የማሽላ ዝርያን ለዓለም አበርክተዋል:: ድርቅን መቋቋም የሚችል የማሽላ ዝርያ ላይ ባስገኙት ውጤት ከአምስት ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ አፍሪካውያን የምግብ ዋስትንን ማረጋገጥ ችለዋል:: ጥናታቸው በዚህ ሳያበቃ በአፍሪካ ምርታማነትን በ40 በመቶ የሚቀንሰው እስትራጋ የሚባለውን አረም መቋቋም የሚችል የተሻሻለ የማሽላ ዝርያን ኢትዮጵያን ጨምሮ ለ12 አፍሪካ ሀገሮች ማቅረብ ችለዋል:: ለእነዚህ እና መሰል የምርምር ሥራዎቻቸው ከ17 በላይ ዓለም አቀፍዊ፣ አህጉራዊ እና ሀገራዊ ሽልማቶችን አግኝተዋል:: እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2009 World Food Nobel Prize የተሸለሙ ሁለተኛው አፍሪካዊ ለመሆን በቅተዋል:: African Nationality Science Hero Award ከተሸለሙ አፍሪካዊ ሰባት ተመራማሪዎችም አንዱ መሆን ችለዋል::

ከሰባ በላይ በሚሆኑ ዓለም አቀፍ እና ሀገራዊ ተቋሞች ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች ላይ የሠሩት የዓለም ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ የዓለም ሕዝብ ቁጥር በጨመረ ቁጥር የምግብ ፍላጎት እየጨመረ ይመጣል ይህን ለመቋቋም ሳይንስ ፣ ቴክኖሎጂ እና የምርምር ፈጠራ ውጤቶች በመጨመር ይሄንን ችግር መቋቋም የግድ የሚል ነው ይላሉ:: ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2011 በፕሬዚዳንት ባራክ አባማ የዓለም አቀፍ የምግብ እና ግብርና ልማት ቦርድ ውስጥ እንዲሁም ከ2014 ጀምሮ በዩናይትድ ኔሽን ሴክሬተሪ ጄነራል ባኒኪሞን የ UN የሳይንስ አማካሪ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ::

ነገርን ነገር ያነሳዋልና እግረ መንገዴን ስለአልተዘመረላቸው የመቀሌው ዩኒቨርሲቲው የግብርና ፕሮፌሰር ላነሳ ወደድሁ። የምማረው ከገበሬ ነው ስለሚሉት ተመራማሪ ፕሮፌሰር ምትኩ ኃይለ። ፕሮፌሰር የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ መሥራች እና የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ዓለም አቀፍ የግብርና ሽልማት አሸናፊ እንደነበሩ ይታወሳል። ዓለም አቀፍ የግብርና እና ላይፍ ሳይንስ ከፍተኛ ተቋማት ማኅበር (GCHERA)ፕሮፌሰር ምትኩ ኃይለ እና የጌንት ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ማርክ ቫን ሞንታጉ የ2021 የዓለም ግብርና ሎሬቶች በማለት ሸልሟቸዋል።

የሽልማቱ ሥነ ሥርዓትም፣ በቻይና ውስጥ በበይነ መረብ የተካሄደ ሲሆን፣ ፕሮፌሰር ምትኩ በአፈር እና ግብርና ልማት፣ በዕፅዋት መዓዛ፣ በአየር ንብረት ለውጥ እና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በሠሯቸው ሥራዎች መታጨታቸው ተገልጿል። መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ባዘጋጀው የእንኳን ደስ አለዎት ፕሮግራም ላይ፣ ፕሮፌሰሩ በኢትዮጵያ “በግብርና፣ የሳይንስ ትምህርት እና ሳይንሳዊ ጥናቶች ላይ ከፍተኛ አስተዋፅዖ” አድርገዋል ብሏል።

በወቅቱ የስልክ እና ኢንተርኔት አገልግሎት በተቋረጠባት የትግራይ ክልል ውስጥ ይገኙ የነበሩት ፕሮፌሰር ምትኩ ኃይለ፣ ‘የ2021 የዓለም ግብርና ሎሬት በመሆን አሸንፈሃል፤ ሽልማቱን የምትቀበል እንደሆን አሳውቀን’ የሚለው የኢሜይል መልዕክት እስከደረሳቸው ዕለት ስለ ሽልማቱን እንደማያውቁ ይናገራሉ። ይሄንን መልዕክት ሲያዩ ‘ማጭበርበር ይሆን?’ ብለው ተጠራጥረው እንደነበር እና መደነቃቸውን ለቢቢሲ ተናግረዋል።

“ኢንተርኔት በማይገኝበት ሁኔታ ውስጥ ምን እየተካሄደ እንዳለ ማወቅ አይቻልም፤ መልዕክቱም ከማላውቀው ሰው ስለሆነ የደረሰኝ ማረጋገጥ ነበረብኝ። አሁን ባለንበት ሁኔታም እንደዚህ አይነት ነገር ስለማልጠብቅ ሽልማቱ አስደንቆኛል”ሲሉ በወቅቱ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

ከ20 ዓመታት በፊት በላቲን አሜሪካ የሚገኘው ኧርዝ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የነበሩ እና አሁን የጂሸራ ሊቀመንበር እና ፕሬዚዳንት የሆኑትን ጆሴ ዛግሉል፣ ሽልማቱ ላይ ፈርመውበታል። ይህንን ሲመለከቱ እውነት ነው ብለው ማመን እንደቻሉ የሚናገሩት ፕሮፌሰር ምትኩ “ወደ ቤት ሄጄ ባለቤቴ እና ልጄን ሳሳያቸው ሁላችንንም አስደነቀን” ይላሉ ፕሮፌሰሩ፣ እስከ አሁን በግል እና ከሌሎች የሙያ አጋሮቻቸው ጋር በመሆን የሠሯቸው ከ200 በላይ የምርምር ሥራዎችን አሳትመዋል። ፕሮፌሰር ምትኩ፣ በ1993 ዓ.ም የመቀሌ ግብርና ኮሌጅ እንዲቋቋም ያደረጉ ሲሆን፣ ከ2000 እስከ 2011 ባሉ ዓመታት ደግሞ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በመሆን አገልግለዋል።

ላለፉት ለ30 ዓመታት በኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አስተዳደር እና የሰው ኃይል ግንባታ እንዲሁም በተፈጥሮ ሃብት እና የአፈር ልማት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያላቸው ፕሮፌሰር ምትኩ ማን ናቸው?ፕሮፌሰር ምትኩ ዕፅዋት እና አረንጓዴ አካባቢን ስለሚወዱ የተፈጥሮ ተሟጋች ናቸው። በሆነ አጋጣሚ ሰዎች ለጥርስ መፋቂያ ነው ብለው ሲቆርጡ፣ ወይም የመንገድ ዳር ማስዋቢያ የሆኑ ሳር እና አበባዎችን ረግጠው አልያም ቀንጥሰው ሲሄዱ፣ ውሃ በቸልተኝነት ሲፈስ ካዩ ይቆጣሉ፤ ይጣላሉ።

የፕሮፌሰሩ የምርምር ሥራዎች የአፈር ለምነትን ማረጋገጥ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። አብዛኛዎቹ ሥራዎቻቸው ትግራይ ላይ ትኩረት ያደረጉ ሲሆኑ፣ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች የሚገኘውን የአፈር አይነት በማጥናት መጀመራቸውን ይናገራሉ። ሕዝቡ ለረጅም ዘመናት ኑሮው ግብርና ላይ ተመሥርቶ ስለኖረ ሰፋፊ የግብርና አካባቢዎች ተሸርሽረው እና ይዘታቸውን ቀንሶ ነበር።

ባለፉት 30 ዓመታትም በተፈጥሮ ሃብት ልማት ከገበሬው ጋር በመሥራት የግብርና ምርትን ማሳደግ፣ የአፈር ለምነት እና የውሃ ምንጮች እንዲጎለብቱ፣ የከርሰ ምድር ውሃ መጠን ከፍ እንዲል፣ የመስኖ እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እንዲያድግ እና የደን ሽፋን እንዲጨምር ማድረግ ተችሏል ብለዋል። ፕሮፌሰር ምትኩ እነዚህ ሥራዎችን ወደ ዓለም አቀፍ መድረኮች በመውሰድ እውቅና እንዲያገኙ ማድረግ ላይ ትልቅ ሥራ አከናውነዋል።

ለዚህም ከአምስት ዓመት በፊት ኢትዮጵያ በትግራይ ክልል በረሃማነት በማጥፋት ላይ በተሠሩ ሥራዎች ተሸላሚ ሆናለች። “እኔ የገበሬን ችግር በማየት ከገበሬው ነው የምማረው፤ እነዚህ ሥራዎችን ከእሱ ተምረን ሳይንስ ጨምረን ስንሰጠው ኑሮውን የሚያሻሽል ለውጥ ማምጣት እንደሚችል አሳይተውኛል። ለውጥ ካላመጡ ደግሞ እኔ የተጠያቂነት ኃላፊነት ይሰማኛል” በማለት ምሑራን የሚሠሯቸው ጥናቶች ኅብረተሰቡን ያሳተፉ መሆን አለባቸው ይላሉ።

**ሻሎም ! አሜን ።**

# የባሕል እመቤቷ ሻምበል ደመቀች መንግሥቱ (ሎሚ ተራተራ)

**እፀገነት አክሊሉ**



ፎቶ- ሳሙኤል ተስፋዬ

ሀገር በተለያዩ ጊዜያትና አጋጣሚዎች ጀግኖችን ታፈራለች:: እነዚህ ጀግኖቿ ደግሞ በተሰማሩበት መስክ ሁሉ የሀገራቸውን ስም ያስጠሩ ሰንደቋም ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ያደረጉ ናቸው:: ታዲያ እነዚህን ጀግኖቿን በሚገባቸው ልክ አክብራለች ወይ ከተባለ መልሱ አላከበረችም ነው:: ምክንያቱም የተለያዩ ዓይነት ማሳያዎችን ማቅረብ ስለሚቻል ነው::

የዛሬዋ የሕይወት ገጽ እንግዳችን ለሀገር ትልቅ ዋጋ ከፍላለች:: በወታደር ቤት ረጅም የእድሜዋን ዓመታት ኣሳልፋለች:: እስከ ሻምበልነትም ደርሳለች:: በኢትዮ ሶማሌ ጦርነት ወቅት ሴትነቷ ሳይገድባት ጦር ሜዳ ድረስ እየገባች ለሠራዊቱ ሞራል የሚሆኑ የጀግንነት ዜማዎችን ከመሥራትም ባለፈ ክላሽ ተሸክማ ተዋግታለች:: በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድም

**.........ሎሚ ተራ ተራ**

**ሎሚ ተራ ተራ**

**ሎሚ ተራ ተራ እናቴን አደራ::** በሚለው ልብ ሰርሳሪ ዜማዋ ትታወቃለች:: ከዚህ ዘፈኗ በኋላም ደግሞ በቪዲዮ ተቀናብሮ የተሠራው ...

**......እኮራበታለሁ በእኔነቴ**

**የጥቁር አንቁ ነው መሠረቴ**

**በኢትዮጵያዊነቴ እኮራለሁ**

**ለማንዴላ ክብር መሠረት ጥያለሁ.....**

በማለት ከትልልቅ የሀገራችን መሪዎች እስከ ኢትዮጵያውያን የቁርጥ ቀን ጀግኖች አርበኞች ድረስ ያወደሰችበት ሙዚቃዋ መለያዋ ነው:: የባሕሏ እመቤት ሻምበል ደመቀች መንግሥቱ (ሎሚ ተራተራ):: እኛም የሀገር ባለውለታነቷን እንዘክር አሁን ያለችበትን አስከፊ የሕይወት ገጽታ አድናቂዎቿ እንዲሁም መላው ኢትዮጵያውያን ያውቁት ዘንድ በዚህ መልኩ አቅርበነዋል::

ሻምበል ደመቀች (ሎሚ ተራተራ) ተብላ ስትጠራ እጅግ ደስ እንደሚላት ትናገራለች:: እኛም በዚሁ ስሟ እየጠራን ታሪኳን እንጽፍ ዘንድ ወደናል::

ሎሚ ተራተራ የተወለደችው ወሎ ክፍለ አገር መካነ ሰላም አውራጃ ነው:: በተወለደችበት አካባቢም ከብት በመጠበቅ ቤተሰቦቿን አቅሟ በቻለው ሁሉ በማገዝ አስፈላጊውን የቤት ሥራ በመሥራት ስለማሳለፏ ትናገራለች::

በእነዚህ የልጅነት ጊዜዎቿም ከብት ስትጠብቅ የቤቱን ሥራ ስትሠራ ብቻ ምን አለፋችሁ ባለፈችበት ባገደመችበት ሁሉ ማንጎራጎር ደግሞ መገለጫዋ ነው:: ይህ እንጉርጉሮ እንጀራዋ እንደሚሆን ግን ምንም አልገመተችም ነበር::

"......እናቴ የትልቅ ሰው ዘር የምትባል ነበረች:: እኔና ወንድም እህቴን በጥሩ ሁኔታ ነበር ያሳደገችን፤ አባታችን በልጅነታችን ነው በሕመም ምክንያት አዲስ አበባ ለሕክምና መጥቶ የቀረው፤ ስለዚህ የልጅነት ጊዜዬን ከእናቴ ጋር ነበር ያሳለፍኩት" ትላለች::

ታዳጊዋ ሎሚ ተራተራም ከእናቷ ቤት ልትወጣ እንደ ሴት ሦስት ጉልቻ ልትመሠርት ጊዜው ደረሰና ሽማግሌ ተላከ ፤ ምንም እንኳን ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ባትሆንም በባሏ እናት ቤት ከባሏ ጋር አብራ ታድግ ዘንድ በሚል ለማደጎ ጋብቻ ተሰጠች:: እሷም በልጅነቷ እናቷን ተለይታ የወደፊት ቤተሰቦቿ ወደሚሆኑት የባለቤቷ እናት ቤት አመራች:: በዛም ከባሏ ጋር እንደ እህት ወንድም ሆነው አብረው እየተጫወቱ የሚሠራውንም እየሠሩ መኖር ጀመሩ::

".......የተዳርኩት በልጅነቴ ነው:: የባለቤቴ እናት ቤትም ገብቼ እንደ ልጅ ከእሳቸው ጋር እየተኛሁ ከእህት ከወንድሞቹ ጋር እየተጫወትኩ አደኩ:: ነገር ግን እኔም እሱም ለአቅመ አዳምና ሄዋን ስንደርስ ጎጆ ቀልሰውልን ጫጉላ ቤት እንድንገባ ሆነ፤ በዚህ ጊዜ ትዳር የያዝኩ ሴት መሆኔ ታወቀኝ፤ በፍጹም ስሜቱን ልቀበለው ከበደኝ:: ስለዚህ ከእሱ ጋር በአንድ ጎጆ ከመኖር ይልቅ ሌሎች አማራጮችን ማየት እንዳለብኝ ወሰንኩ" በማለት ትናገራለች::

እንዳሰበችውም አልቀረችም ከዛ ጫጉላ ቤት እየጠፋች በየጫካው ዛፍ ላይ ሳይቀር ማደር ጀመረች:: ብትመከረም ቢቆጧትም እንዲህ አይደለም ትለምጂዋለሽ ቢሏትም እሷ ግን አሻፈረኝ እንዳለች ቀረች:: አንድ ሌሊት ዋርካና ዋርካ መሐል ስታድር የመጡባትን ጅቦች ስታስብ አሁንም ድረስ ይዘገንናታል:: እንዲህ በማስቸገሯ የባሏም ቤተሰቦች ተከፉ፤ እሷ ግን ሁኔታው ግድ አልሰጣትም እንደውም ራቅ ብለው ወደሚገኙት እናቷ መሄድ እንዳለባት ወሰነች::

".....እዛ ዋርካ ዛፍ ላይ ተንጠልጥዬ እነዛ ሁሉ ጅቦች በላዬ ሲዞሩ ካደሩ በኋላ በቀጥታ እናቴ ጋር መሄድ አለብኝ ብዬ ነው የወሰንኩት፤ እናም ሲነጋ ያንን ሁሉ መንገድ በሩጫ አቋርጬ ስሄድ ባለቤቴ ከኋላ ቢከተለኝም ማንም ሊደርስብኝ ሳይችል እናቴ ቤት ደረስኩ"::

ሎሚ ተራተራ እናቷ ጋር እያለከለከች ከገባች በኋላ በቀጥታ የተናገረችው ".....ከዚህ በኋላ ባል ቤት ሂጂ የምትይኝ ከሆነ ቦተር (በአገራቸው ትልቅ ወደሆነው ገደል) ራሴን እጨምራለሁ "በማለት ከመናገሯም በላይ አዲስ አበባ ወደሚገኙት አባቷ ዘንድ መሄድ እንደምትፈልገም ትናገራለች:: እናት የልጃቸው ሁኔታ ምንም ስላላማራቸው "እባክሽ ልጄ ትተሽኝም አትሂጂ የፈለግሽውን አደርገልሻለሁ ከብትም እሰጥሻለሁ፤ መሬትም ይቆረስልሻል ልብስም እገዛልሻለሁ" በማለት ልመናቸውን አቀረቡ፤ እሷ ደግሞ አንዴ ቆርጣለችና ምንም ቢመጣ አይሆንም እንደውም አባቴ ጋር ነው መሄድ እፈልጋለሁ በማለት በአቋሟ ጸናች:: እናትም በሁኔታዋ በጣም ስለተበሳጩ ተስፋም ስለቆረጡ በቃ ከበግ ነጋዴዎች ጋር በእግሯ አዲስ አበባ ትግባ ብለው እንደላኳት ትናገራለች::

".......እናቴ እባክሽ ልጄ ጥለሽኝ አትሂጂ ብላ ብዙ ለመነችኝ:: እኔ ግን እምቢ አልኳት:: እረግምሻለሁ እንኳን ብትለኝ ልሰማት አልፈለኩም:: እሷም በጣም ስለተናደደች በእግራቸው ከሚሄዱ በግ ነጋዴዎች ጋር ላከችኝ፤ በዚህም ሰባት ቀን ሙሉ በእግሬ ተጉዤ ጎሐ ጽዮን ስደርስ መንቀሳቀስ አቃተኝ:: ሰዎቹም በጣም ተደናግጠው መኪና ለምነው በማሳፈር አዲስ አበባ እንድገባ አገዙኝ" ትላለች::

አዲስ አበባ ከተማም ስትገባ ለሕክምና ብለው ከሀገራቸው የወጡት አባቷ ልደታ ቤተክርስቲያን አካባቢ ይኖሩ ነበርና ወደሳቸው አመራች:: አባቷም ሲያዩት በጣም ቢደናገጡም ልጃቸውን ስላገኙ ደግሞ ደስታም ተሰማቸው:: ግን ደግሞ እሳቸው ባላሰቡት ሁኔታ ሀገራቸውን ጥለው መምጣታቸው የሁልጊዜ ቁጭታቸው ነበርና ልጃቸውም የእሳቸው አይነት እድል እንዲደርሳት ፍጹም አልፈለጉም፤ በዚህም "... እባክሽ የእኔ ወጥቶ መቅረት ይበቃል አንቺ እንኳን ሀገርሽ ግቢ" በማለት ለመኗት:: ሎሚ ተራተራ ግን የመማር ፍላጎት ነበራትና "....ሀገሬ አልመለስም ከቻልክ ትምህርት ቤት አስገባኝ" በማለት እሷም የራሷን ሀሳብ እየሰነዘረች ቀናት ተቆጠሩ::

ሎሚ ተራተራ አዲስ አበባ ልደታ ሰፈር ላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው ታዋቂ የሆነችው፤ የመንደሩ ሰው ሁሉ ወደዳት:: እሷም እንደ ሀገሯ እያንጎራጎረች ከአካባቢው ሕጻናት ጋር ነበር የምትውለው፤ በተለይም እንጉርጉሮዋ ብዙዎች ይማረኩ ነበር:: ከአባቷ ጋር ሥራ የሚሠሩ የልብ ጓደኞቻቸው ታዳጊዋንና የሙዚቃ ፍቅሯን እንዲሁም ስታዜም ያላትን ችሎታ ተመልክተው ለአባቷ ".....ይህችን ልጅ ብሔራዊ ቲያትር ቤት ለምን አናስቀጥራትም" በማለት ሀሳብ አቀረቡ:: አባት ድምጿን የሰሙት በችሎታዋም የሚተማመኑ ቢሆኑም ሀሳቡን ግን ነገሬ ብለው መቀበልን አልፈለጉም:: ጓደኞቻቸው ደግሞ መቀጠር አለባት በማለት ይዘዋት ብሔራዊ ቲያትር ቤት ሄዱ::

"........የአባቴ ጓደኛ እንደተመኙ አልቀሩም ብሔራዊ ቲያትር ቤት ይዘውኝ ሄዱ:: አቶ አውላቸው ደጀኔ ደግሞ "ሎሚ ተራተራ" የሚለውን የዘፈን ግጥም እንዳጠና ሰጡኝ:: ምክንያቱም ይህ ግጥም ለሌሎችም ተሰጥቶ ነበርና የተሻለ የተጫወተውን ለመምረጥ እንዲመቻቸው ነው:: በዚህ መሠረትም እኔ የተሰጠኝን ግጥም በደንብ አድርጌ አጥንቼ ዜማውም በደንብ ገብቶኝ ዘፈንኩት፤ እነሱም በጣም ወደዱት ለሬዲዮም ለቴሌቪዥን እንጨት አዝዬ እየዘፈንኩ ተቀረጽኩ ፤ ከዛማ በቃ ደስተኛ ሆንኩ፤ ዛሬም መጠሪያ ስሜ ሆነ" ትላለች::

በወቅቱ ብሔራዊ ቲያትር ቤት በጊዜያዊ ሠራተኝነት በ60 ብር ደመወዝ ቀጠራት:: ነገር ግን አሁን ለእኛ ልትገልጽልን ባልፈለገችው ምክንያት ከስድስት ወራት የሥራ ቆይታ በኋላ ተቀነሰች:: ለሥራው ከፍ ያለ ጉጉት የነበራት በመሆኑ መቀነሷ እጅግ ቢያሳዝናትም ተስፋ ግን አልቆረጠችም:: ከምንም በላይ ደግሞ ሎሚ ተራተራን ስትዘፈን የወደዷት ባለሙያዎች ሌሎች እድሎችን እንድታገኝ አመቻቹላት፤ በዚህም ዶክተር ተስፋዬ አበበ ጋር ምሥራቅ በረኛ ፖሊስ እንድትገባ ሆነና ኑሮዋን ከአዲስ አበባ ወደሐረር አደረገች::

**ሐረርና ሎሚ ተራተራ**

በሥራ አጋጣሚ የሄደችባት የሐረር ከተማ በፍጹም ፍቅርና አክብሮት ነበር የተቀበለቻት:: የሐረርን ሕዝብ ፍቅር አብሮ የመብላት የመተዛዘን ብሎም አብሮ የማደግ ፍላጎቱን ተናግራ አትጠግብም::

" ....ሐረር ከትወልድ መንደሬ የበለጠ የምወደው ብዙ የእድሜዬን ክፍልም የኖርኩበት በርካታ ወዳጆችን ያፈራሁበት፤ የተዳርኩበት ፤የወለድኩበት፤ ብቻ ብዙ መልካም ነገሮችን ያየሁበት ከተማ ነውና መቼም ቢሆን ከልቤ አይጠፋም" በማለት ትገልጻዋለች::

ሎሚ ተራተራ ሐረር ፖሊሲ በሲቪል የተቀጠረች ቢሆንም ወዲያው ወደሚሊተሪ ይዙሩ በመባሉ በቶሎ ነበር ወታደር የሆነችው:: ከሁሉም በላይ ደግሞ ወቅቱ ሶማሌ ሀገራችንን የወረረችበት ጊዜ ነበርና እነ ሎሚን ጨምሮ ሁሉም ሀገሬው ራሱንና ሀገሩን ከጠላት ለመከላከል ወታደር መሆንም የውዴታ ግዴታው ነበር:: ሎሚ ይህም ሁኔታ ቢሆን ለእሷ አስደሳች ነበር፤ ከሀገር ከወገን ከዳር ድንበር በላይ ምን አለ ብላ የወሰደቻትን መጠነኛ የውትድርና ሥልጠና አጋዥ አድርጋ ከሠራዊቱ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## የባሕል እመቤቷ ሻምበል ....

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

ጋር በሄደበት እየሄደች፤ በሙዚቃ ሥራዋ እያበረታታች አስፈላጊም ሲሆን ውጊያ ውስጥ ገብታ ዘራፍ ብላ እየተዋጋች ጀግንነቷን ያስመሰከረች እንስት ናት::

"....በወቅቱ አሁንም ድረስ በጣም የሚያስደስተኝ ነገር እንኳን ወታደሩ ጋር መላው ሕዝቡ ጋር ለእኔ የሚል ወይም ሌብነት የሚባል ነገር አለመኖሩ ነው:: ሙስናማ ስሙም አይታወቅም :: በጣም የሚገርመው ነገር ሶማሌ ጅግጅጋን አስለቅቃ ወደሐረር ስትመጣ ሁላችሁም ራሳችሁን አድኑ ተብሎ የምንችለውን ሁሉ ስናደርግ እኔና አንድ ሌላ ድምፃዊ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሄደን በጆንያ ገንዝብ አውጥተን መኪና ላይ ሲጫን እንድንጠብቅ ታዘዝን:: በጣም የሚገርመው ወቅቱ የግርግር ቢሆንም እኛ ጠባቂዎቹ ሆንን የባንክ ቤቱ ሠራተኞች ፍጹም የሀገራቸውን አደራ ለመዝረፍ ሀሳቡ እንኳን አልነበራቸውም:: ሌብነት የሚባል ነገር የለም፤ አደራን በተባለው ቦታና ጊዜ ለማስረከብ ብቻ ነው ሩጫው:: እና እኛም የተጣለብንን ኃላፊነት በአግባቡ ተወጥተናል" በማለት ትናገራለች::

እነ ሎሚና ሌሎች የሠራዊቱ አርቲስቶች በወቅቱ ሶማሌን ድባቅ ለመምታት እየተንቀሳቀሰ ለነበረው ሠራዊት ደጀን ሆነው በሄዱበት ሁሉ ሄደዋል፤

### ......የሀገሬ ጎበዝ ምን ወንዱ ብቻ

**ሴቷም ብትሆን የላትም አቻ** ...እያሉ እያዜሙ ተከትለው "ፈዲስ" ገቡ :: ከዛም 34 ተኛው ፓራ ኮማንዶ እየዘፈነ መጣ:: ሁለቱም በአንድ ገጥመው ሶማሌን እያሯሯጡ ወደመጣችበት ሸኟት::

ሶማሌም በመጣችበት እግሯ ተሸኘች ሎሚና ጓደኞቿም በወታደር ቤት የሙዚቃ ሥራቸውን እየሠሩ ኑሮን ቀጠሉ:: ሎሚም ከምትወደው የሐረር ሕዝብ ጋር እየኖረች ነው:: የዳሯት የኳላት የሐረር ጓደኞቿ ናቸው::

".......ሐረሮች ጀግኖች፣ ባለሙያዎች፣ ለሰው አሳቢዎች፣ አብሮ መብላት የሚያውቁ፣ የእምነት፣ የብሔር ልዩነትን የሚጸየፉ በጠቅላላው ሰውን ሰው በመሆኑ ብቻ የሚያከብሩና አብረው መኖርን ቀለል አድርገው የሚያዩ ምርጥ ሕዝቦች ናቸው" በማለት ትገልጻቸዋለች::

ሎሚ ትዳር ከመያዟ በፊት ጓደኛ ነበራት አገባዋለሁ ብላ አስባለች፤ ነገር ግን የእህል ውሃ ጉዳይ ሆኖ ፍጹም ባልገመተችው ይሆናልም ብላ ባላሰበችው መልኩ የልጇን አባት ባለቤቷን ተዋወቀች፤ ተዋውቃም አልቀረች አግብታው የልጅ እናት አደረጋት:: ሎሚ ሁኔታውን ስታስታውሰው በጣም ትገረማለች:: ጭው ብላም በሀሳብ ወደኋላ ትመለሳለች ፊቷ ላይ ኃዘን ይነበባል::

"......... ያገባሁት በጣም ትልቅ ወታደር፤ በጣም የሚፈራ እሱ በተቀመጠበት ቡና ቤት ሌሎች ለመግባት የሚሳቀቁለት አይነት ሰው ነበር:: መጀመሪያም ለትዳር ሲጠይቀኝ እምቢ ብዬ ነበር፤ ኋላ ላይ ግን በግድም በውድም ተስማምቼ ወደ ትዳር ከገባሁ በኋላ ትዳሬ በጣም የጣፈጠ ያማረ ሆነ፤" በማለት ትገልጻለች::

ሎሚ ከትዳሯ አንድ ልጅ ወልዳለች፤ የእህቷን ልጅም እንደራሷ ልጅ አድርጋ አሳድጋለች:: ባለቤቷ ትልቅ የጦር መሪ ነበርና በዋለበት ግዳጅ ሁሉ ድል የእሱ ናት፤ በዚህም ምክንያት ከትዳሩ ጋር አብሮ የመቆየት እድልን አላገኘም:: ወዲያውም በግዳጅ ወደ ተለያዩ ቦታዎች ተላከ እሷም አንዳንድ ቦታዎች ላይ ብታገኘውም ለመጨረሻ ግዳጅ የተላከበት ቦታ ላይ ግን ማግኘት አልቻለችም::

".........ባለቤቴ ከውትድርና ብቃቱ ባሻገር ጦር ሠራዊቱን ወክሎ መረብ ኳስ (ቫሊቦል) ይጫወት ነበር፤ በዚህም ቀብሪደሐር ላይ ለውድድር እመጣለሁ እና እንገናኛለን ብሎኝ እየጠበኩት ሳለሁ የወታደራዊው ደርግ መሪ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ኤርትራ ተከባለችና ግዳጅ ሂዱ በማለታቸው በዛው ሄደ፤ እኔም ከዛ በኋላ ተስፋ ቆረጥኩ" በማለት ልብ በሚሰብር ኃዘን ሁኔታውን ታስታውሳለች::

ሎሚና ሌሎች ጓደኞቿ እንዲሁም መላው የደርግ ሠራዊት የመንግሥት ለውጡን ተከትሎ በተፈጠረው መበተን ኑሯቸው አስከፊ ደረጃ ላይ ደረሰ:: ሎሚም ባለቤቷ ያለበትን ሁኔታ አታውቅም ልጅ ይዛለች ደመወዝ የለም፤ ሥራ የለም ብቻ ነገሩ ሁሉ ተገለባብጧል፤ ይህንን ሕይወት አይታው አታውቅም ምን እንደምታደርግ ግራ ገባት የመጨረሻ ውሳኔዋ ወደማያውቀኝ ሀገር ማለትም

**አንድ ሌሊት ዋርካና ዋርካ መሐል ስታድር የመጡባትን ጅቦች ስታስብ አሁንም ድረስ ይዘገንናታል**



አዲስ አበባ ገብቼ ለምኜ ልጄን ላሳድግ የሚል ሆነና ቤት ንብረቷን ጥላ ለእሷና ለልጇ የሚለብሱትን ይዛ አዲስ አበባ ገባች::

አዲስ አበባ ላይ ከመጣች በኋላ ልደታ አካባቢ ባለችው እስከ አሁንም በምትጠለልባት አራት በአራት ቤት ውስጥ ከአንድ ወንድምና እህቷ እንዲሁም ከአባቷ ጋር ልጅ ይዛ ተጨመረችባቸው:: ይህ ኑሮ ደግሞ ለሁሉም አልተመቸም እንደልብ እንኳን እግር ዘርግቶ መተኛትን አላስቻለም:: ከሁሉም በላይ ደግሞ የእሷ ልጅ ባጋጠመው ድንገተኛ ሕመም እንደልቡ መንቀሳቀስ መውጣት መግባት አለመቻሉ ኑሮን የበለጠ አስከፊ አደረገው ::

የወደቀን ዛፍ ምሳር ይበዛበታል! እንዲሉ ሎሚ በመንግሥት ለውጥ ምክንያት ያጋጠማት መፈናቀል ብዙ ነገሮችን አሳጥቷታል፤ ከምንም በላይ የጣመ የጣፈጠ ትዳሯን አፍርሶባታል፤ ".......አንዳንድ ጊዜ ችግር ሲመጣ ይደራረባል፤ እኔና ባለቤቴም ተደራራቢ ችግር ነው የገጠመን፤ ለእናት ሀገራችን ብዙ ዋጋ የከፈልን ብሆንም መጨረሻችን ግን አላማረም ፤ በተለይ ባለቤቴ ቆስሎ ከግዳጅ መጥቶ አዲስ አበባ ሜዳ ላይ ተኝቶ ነው ያገኘሁት፤ ከሐረር ይዤው የመጣሁትን የሚሊተሪ ብርድ ልብስ ለሁለት ተካፍለን ደጋጎች የሚሰጡኝን ገንዘብ ይዤ 15 ብር ቤት ተከራይቼ ነበር ያስቀመጥኩት፤ ነገር ግን በእስትንፋሱ መጨረሻ ላይ ከልደታ የሺ ደበሌ የሚባለው ሰፈር መሄጃ የትራንስፖርት 5 ብር አጥቼ ባለቤቴን ቆሜ ሳልቀብረው ቀረሁ" በማለት አስከፊውን የችግሯን ጅማሮ ትገልጻለች::

ሎሚ የደረሰባት ችግር ከባድ ነው:: ከዛም አልፎ ማንም ከጎኗ የሌላት እና ይህንን በዚህ አድርጊው፤ በሙያሽ ይህንን ብትሠሪ ብሎ የሚያማክራት አንድም ሰው ባይኖራትም በተለይም የሙዚቃ ሙያዋን ለመቀጠል ብዙ ጥረቶችን አድርጋለች ስኬታማነቱ ላይ ግቡን ባይመታም ::

መልካሙ የሚባል የሙዚቃ ማቀናበሪያ ስቱዲዮ ያለው ግለሰብ ታሪኳን የሚያውቅ በመሆኑ "እኮራበታለሁ" የሚል ሥራ ሠርቶላት "ጋራ ዩቱብ" ለሕዝብ ጆሮ አድርሶላታል:: እንቁጣጣሽ የሚል ሙዚቃንም እንድትሠራ አግዟታል:: በቀጣይም ከሊፕ እንደሚሠራላት ቃል የገቡላት መኖራቸውንም ትናገራለች::

ሎሚ ከዛሬ 26 ዓመት በፊት ሙሉ የካሴት ሥራ ሠርታ ነበር፤ ነገር ግን ሥራዋ ተጠናቆ ፖስተሩ ሲለጠፍ ሙዚቃ ቤቶች ፈረሱ፤ ይህ ብቻ አይደለም በወቅቱ የአርቲስት አስቴር አወቀ ዘፈን ወጣና የእሷ ሙዚቃ ተዋጠ በዛም የትኛውም ሥራ ሳይሰማ ቀረ:: ሎሚ በዚህ ሁኔታ በጣም ልቧ ተሰብሮ ይህንን ትላለች:: "....... በወቅቱ አጋጣሚው ጥሩ አልነበረም ፤ እኔ ለሁሉም ሚዲያዎች እየዞርኩ ሙዚቃው በሬዲዮ እንኳን እንዲሰማ ሰጥቻቸው ነበር፤ ነገር ግን ሚዲያው ያዳላል፤ አንዳንድ ጊዜ መንገዱ ራሱ ምን እንደሆነ ለማወቅ ይቸግራል:: ቀኑን ሙሉ ሬዲዮም ሆነ ቴሌቪዥን ብትሰሚ የአንድ ሰው ሙዚቃ ከአምስትና ስድስት ጊዜ በላይ ይለቀቃል:: እኔ የራሴን ዘፈን በአንዱም ጣቢያ ላይ አዳምጬው አላውቅም:: እናም እንደእኔ ግምገማ ለሕሊናው የሚሠራ ሰው የለም:: ይህ አካሄድ ደግሞ እኔን ጨምሮ ብዙዎችን ቀብሮ ቀርቷል፤ በጣም ያሳዝናል" በማለት ቅሬታዋን ትገልጻለች::

ሎሚ የባሕል ዘፋኝ እንደመሆኗ በተለይም በፈንድቃ የባሕል ቤት ሥራዎችን አልፎ አልፎ ትሠራ ነበር፤ ነገር ግን ዘላቂ ባለመሆኑ አሁን ላይ አቁማለች:: ውለታዋንና ያለችበትን ሁኔታ ተገንዝቦ ኑሮ እንዳይከብዳት ያግዛት የነበረው ሙዚቀኛ ማዲንጎ አፈወርቅ ነበር:: ከእርዳታውም ባሻገር የጦር ሜዳ ዘፈኖቿን በካሴት ደረጃ ለመሥራት እየተዘጋጀ ባለበት ወቅት ነው ሞት የቀደመው:: አርቲስት ዓለማየሁ እሸቴም በተመሳሳይ ሰዎችን እያስተባበረ ይረዳት ነበር:: አሁን ሁሉም የሉም፤ ሎሚ ግን ከችግሮቿ ጋር አብራ አለች::

ሕዝቤ አላወቀኝም፤ መንግሥት ግን ወቀሳ ይገባዋል የምትለው ሎሚ፤ የቀድሞ ሠራዊት ለሀገሩ የተዋደቀ ነው:: ምናልባት መጥፎ ሥራም ሠርቶ ይሆናል ግን ደግሞ ጥሩም መጥፎም የሆነው ለሀገር ነውና ሁሉንም በልኩ አይቶ ማስቀመጥ ይገባል:: የሆነውና እየሆነው ያለው ነገር ከባድ ብሎም አሳፋሪ ነው::

### አስከፊው የሎሚ አሁናዊ ኑሮ

ልጄ ለብዙ ልጆች ምሳሌ ነበር፤ የሚያውቁኝ ሁሉ ልጅ ከተወለደ እንደሎሚ ልጅ ነበር የሚሉት፤ በጣም ጨዋ በትምህርቱ ጎበዝ ነበር፤ ምን ዋጋ አለው በስተመጨረሻ በማናውቀው ምክንያት ተበላሸብኝ:: እኔም በደጄ እንኳን ሻይ አፍልቼ አልሸጥ ነገር ቤቴ እንኳን ለንግድ እግር ዘርግቶ ለመተኛት አይበቃም:: ቀኑን ሙሉ አእምሮዬ ሲረበሽ ይውላል ፤ አንዳንድ ጊዜ መኖሬ ያስጠላኛል፤ መለስ ብዬ ሳስብ ደግሞ ልጆቼስ እላለሁ::

እኔ አሁን የምመኘው ሰፋ ባለ ቤት ውስጥ አልጋ ላይ እንደልቤ ዧ ብዬ ተኝቼ በማግስቱ መሞትን ነው:: የሚገርምሽ ከዛሬ 21 ዓመት በፊት ጀምሮ ቤት እንዳገኝ በተለያዩ አካላት የተጻፈልኝ ደብዳቤ አለ:: ግን እህ ብሎ የሚሰማ ሥራ አስፈጻሚ ስለሌለ እስከ አሁን ተፈጻሚ አልሆነም በማለት ከፍ ባለ ኃዘን ትናገራለች::

ሎሚ በዚህን ያህል ደረጃ ኑሮ የከበዳት፤ ጓዳዋ ባዶ የሆነና ጎኗን ማሳረፊያ አይኑራት እንጂ በአቅሟ የበርካታ ድሆችም መጠለያ ነች:: እሷ ቤት መጥቶ ያለውን በልቶ ቡና ጠጥቶ ተስተናግዶ ባለችው አነስተኛ ቦታ ላይ አርፎ የሚሄድ አልፎ ሂያጅ ብዙ ነው በዚህም በጣም ደስተኛ ናት::

".......እኔ የማውቀውም የማላውቀውም ብቻ ማረፊያ ያጣ ሁሉ ይመጣል፤ እውነት ለመናገር ያለ እንግዳ አድሬ አላውቅም:: የሚተኙበት ሳጣ ግን በጣም እናደድና ፈጣሪዬንም ለምንድነው እንደዚህ የምትፈትነኝ እለዋለሁ:: አንዳንድ ጊዜ ሰው ስለሚበዛብኝ ራስሽን ሁሉ አጥፊ አጥፊ የሚለኝ ጊዜ አለ:: ነገር ግን ቤቴ የድሃ ቤት ነው" በማለት ትናገራለች::

ሎሚ ዛሬ ላይ የምትፈልገው በሙያዋ ሠርቶ መኖርን ነው:: ለእኛም እንዳስደመጠችን ድምጿ ገና ብዙ የሚያሠራት ነው:: ስለዚህ በሙያው ያላችሁ ይህችን የሀገር ባለውለታ ሠርታ ኑሮዋን የምትደጉምበትን መንገድ ታመቻቻላችሁ ብለን እናስባለን:: በሌላ በኩልም በምትኖርበት ወረዳም ሆነ ሌሎች ወረዳዎች ወጥታ ወርዳ የሀገሯን ዳር ድንበር ላስከበረች አሁን ደግሞ ከሕመምተኛ ልጅ ጋር በችግር እየተሰቃየች ያለችን ምስኪን ወታደር ማረፊያ በመስጠት ትተባበራላችሁ ብለንም ተስፋ እናደርጋለን:: ለሚደረገው ትብብር ሁሉ እያመሰገንን ሎሚን ማግኘት የሚፈልግ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልን መጠየቅ እንደሚችልም ለመግለጽ እንወዳለን::

# በቱሪዝም ሀብቶች - የአዲስ አበባ ከተማ ድርሻ

ዳግም ከበደ

የኢትዮጵያ መንግሥት ቱሪዝም ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት የሚኖረውን ድርሻ ለማሳደግ ልዩ ልዩ ስልቶችን በመንደፍ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። በዚህ መነሻም በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዋና ዋና ምሰሶ ከሆኑ ዘርፎች አንዱ ቱሪዝም ተደርጓል። አዳዲስ ማስፈፀሚያ ሕጎችን፣ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን እና የልማት እቅዶችን በማውጣትም የዘርፉን አቅም ለማሳደግ እየተሠራ ስለመሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ።

በዋናነትም ኢትዮጵያ ያላትን የመስህብ ሀብቶች በማስተዋወቅ፣ የመዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶችን በማስፈፀም ከዓለም አቀፍ የቱሪስት ፍሰት ድርሻ ተጠቃሚ ለመሆን እየተሠራ ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በመንግሥት በኩል በዘርፉ እየተተገበሩ ያሉ የመዳረሻ ልማት ሥራዎችም የዚሁ እቅድ አካል ናቸው።

የኢትዮጵያን የቱሪዝም መስህቦች ከማልማትና ከመጠበቅ ባሻገር የማስተዋወቅ ተግባር በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ሀብቶቹን ከሀገር ውስጥ ጀምሮ ለመላው ዓለም ማስተዋወቅ የቱሪስት ፍሰትን ጭምሮ ኢኮኖሚያዊ አቅምን ለማሳደግ ይረዳል። በዚህ ረገድ መንግሥት ተገቢ ያላቸውን ስልቶች ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። ከእነዚህ ውስጥም በዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽኖች፣ ኮንፍረንሶች እና ልዩ ልዩ መድረኮች ላይ በመገኘት የኢትዮጵያን የቱሪዝም የመስህብ አማራጮች ማስተዋወቅ አንዱ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም በሀገር ውስጥ ትላልቅ ዓውደ ርዕዮችን፣ ኮንፍረንሶችን እና የንግድና የባዛር ትርኢቶችን በማዘጋጀት የገበያና ትውውቅ ሥራ ያከናውናል። እነዚህን መድረኮች በዲጂታል አማራጭና በመገናኛ ብዙኃን በማሰራጨትም ኢትዮጵያ ያሏትን የቱሪዝም ሀብቶች ተደራሽ በማድረግ የጎብኚዎችን ቁጥር ለማሳደግ እየተሠራ ነው።

በያዝነው የ2016 በጀት ዓመት የቱሪዝም ሀብቶችን ከማስተዋወቅ አንፃር ልዩ ልዩ መድረኮች ተካሂደዋል፤ እየተካሄዱም ይገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ የቱሪዝም ሚኒስቴር በሳይንስ ሙዚየም እያካሄደ ያለው ለአንድ ወር የሚዘልቅ ዓውደ ርዕይ አንዱ ነው። በመላው ሀገሪቱ ያሉ የኢትዮጵያ የቱሪዝም ሀብቶችን በአንድ መድረክ ላይ በማምጣት ሲያስተዋውቅ የቆየው ይህ ዓውደ ርዕይ የፊታችን ጥቅምት 28 ይጠናቀቃል።

ከዚህ በተጨማሪ ባሳለፍነው መስከረም ወር ላይ የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን በስካይ ላይት ሆቴል ያዘጋጀው ዓውደ ርዕይ በአፍሪካ ሀገሮችና በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የቱሪዝም ባለድርሻዎች የተሳተፉበትና በዲጂታል ማስተዋወቅ ረገድ ውጤት የታየበት ነበር። እነዚህ መድረኮች አገሪቱ በተፈጥሮ፣ በታሪክ፣ በባሕልና በልዩ ልዩ የመስህብ ሀብቶች ያላትን አቅም ለማሳየት አስችለዋል።

ከላይ ካነሳናቸው የቱሪዝም ሀብት ማስተዋወቅ (visibility) ተግባሮች በተጨማሪ ተከታታይነት ያላቸው ተመሳሳይ ዝግጅቶች እየተደረጉ ነው። ከእነዚህ ውስጥ ተጠቃሽ የሆነው ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማን የቱሪዝም ሀብቶች የሚያሳየውና የዓለም የቱሪዝም ሳምንትን ምክንያት በማድረግ በመስቀል አደባባይ ለሦስት ቀን የተዘጋጀው መርሐ ግብር ነው።

ይህ መድረክ ኢትዮጵያ በተለይ ደግሞ አዲስ አበባ ያላትን የቱሪዝም ሀብቶች ከማስተዋወቅ ባሻገር ሀብቶቹን ወደ ኢኮኖሚያዊ አቅም "እንዴት ማሳደግ ይቻላል" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሞከረ ስለመሆኑ ተመልክተናል። በተለይ በአዲስ አበባ ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት በዘርፉ የተመዘገቡ ስኬቶች እንዲንፀባረቁበት ተደርጓል። የዛሬው የባሕልና ቱሪዝም አምዳችን በዛሬው ባሕልና ቱሪዝም ዓምዱ በአዲስ አበባ ከተማ ባለፉት ዓመታት የተገኙ ውጤቶች ምን እንደሚመስሉ ይመለከታል።

የአዲስ አበባ ከተማን የቱሪዝም ሀብቶችና እየተሠሩ ያሉ ተግባራት ለማሳየት በማሰብ በመስቀል አደባባይ በቱሪዝም ሳምንት ዝግጅት ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባና የሥራ ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር ዓባይ ከተማዋ አያሌ የቱሪስት መዳረሻዎች ባለቤት መሆኗን ጠቅሰው፣ መስህቦቹን በአግባቡ በመለየት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመራጭ ከተማ እና የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ የሁሉንም ርብርብ እንደሚጠይቅ አመልክተዋል። ኢትዮጵያ ካሏት ሰው ሰራሽ፣ ተፈጥሯዊና ታሪካዊ መስህቦች በተጨማሪ አዲስ አበባ ከተማ ወደ ቱሪስት መስህብነት እየተለወጠች እንደሆነና ከነበረችበት በእጥፍ ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውንም ይገልፃሉ።





የቱሪዝም ሳምንቱ ለሦስት ቀናት በፎቶ ኤግዚቢሽንና በተለያዩ ዝግጅቶች ተከብሯል

**ከተማዋ የአያሌ የቱሪስት መዳረሻዎች ባለቤት ናት። መስህቦቹን በአግባቡ በመለየት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመራጭ ከተማ እና የቱሪዝም መዳረሻ እንድትሆን የማድረጉ ሥራ የሁሉንም አካላት ርብርብ ይጠይቃል።**

እየተከናወኑ ከሚገኙ የልማትና የማስተዋወቅ ሥራዎች መካከል በምሳሌነት አዲስ አበባ የነበራትን የአረንጓዴ ሽፋን ከሁለት ነጥብ ስምንት በመቶ ወደ 15 በመቶ በማሳደግ ከተማዋን ከአየር ንብረት መዛባት በከፍተኛ ሁኔታ መታደግ የሚቻልበት ሁኔታ መፈጠሩን ይገልፃሉ። በዚህም ልዩ ልዩ መዳረሻዎችንና ፓርኮችን በማልማት ውጤታማ ሥራ መከናወኑንም ተናግረዋል። በቱሪዝም ዘርፍ ብዙ ያልተሠራና እምቅ አቅም እንዳለ በማንሳት ሃብቶቹን ማወቅና ማልማት እንደሚጠበቅም አስገንዝበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አፈጉባኤ ወይዘሮ ቡዜና አልቃድር አዲስ አበባን ከቱሪስት መተላለፊያነት ወደ ቱሪስት መዳረሻነት ለመቀየር በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውንና እየተሠሩም እንደሚገኙ ይናገራሉ። አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የአንድነት ፓርክ፣ የእንጦጦ እና የሸገር ፓርኮች እንዲሁም ግንባታው በፍጥነት እየተጠናቀቀ ያለው የአዲስ አፍሪካ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽንና ኤግዚቢሽን ማዕከል የዚህ ማሳያ መሆናቸውን ያነሳሉ። በከተማችን ብሎም በሀገራችን ያሉትን እምቅ የቱሪዝም አቅሞችን በማልማት ወደ ቱሪዝም መስህብነት ለመቀየር፣ የለሙትን የቱሪዝም መስህቦችን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጎብኚዎች በማስተዋወቅ ወደ ውጭ ምንዛሪ ለመቀየር የእያንዳንዱ ባለድርሻ አካልን ንቁ ተሳትፎ እንደሚጠይቅም ይገልፃሉ።

እንደ አፈ ጉባኤዋ ገለፃ፤ በከተማችን የሚገኙ የቱሪስት መስህቦችን በማልማት፣ የውጭ ጎብኚዎች በከተማዋ ያላቸውን የቆይታ ጊዜ በማራዘምና ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ ይገባል። በተጨማሪም የከተማዋ ነዋሪ በቂ የመናፈሻና የመዝናኛ ስፍራ እንዲኖር እየተሰሩ ባሉ ስራዎች በመሳተፍ፣ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ለትውልድ የሚተርፍ አሻራ ለማሳረፍ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ አስተላልፈዋል።

የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሣው በበኩላቸው "የከተማችንን የቱሪዝም ሃብቶች በማስተዋወቅ ሁላችንም የዘርፉ ባለቤቶችና አምባሳደሮች መሆን ይጠበቅብናል" ብለዋል። ዶክተር ሂሩት እንደሚሉት፤ መላው የከተማዋ ነዋሪ በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ የቱሪዝም ሀብቶችን ጠንቅቆ በማወቅ ሁሉም የከተማዋ የቱሪዝም አምባሳደር በመሆን አዲስ አበባ ጽዱ፣ ውብና ለጎብኚዎች የተመቸች ከተማ እንድትሆን አበክሮ መሥራት ይጠበቅበታል።

በርካታ ሀገሮች ቱሪዝምን የውጪ ምንዛሪ ምንጭ በማድረግ መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግርና ለውጥ ለማረጋገጥ የሚያስችል ከአገልግሎት ዘርፍ ውስጥ ቀዳሚውን ድርሻ የሚወስድ ኢንዱስትሪ አድርገውታል ሲሉ ጠቅሰው፣ ይህንን አቅም መጠቀም እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ባሕል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ሃፍታይ ገብረእግዚአብሔር የአዲስ አበባን እምቅ የቱሪዝም ሀብቶች ለማስተዋወቅና እየተሠራ ያለውን ሥራ ለማሳየት የተዘጋጀውን መድረክ አስመልክቶ እንዳሉት፤ የቱሪዝም ዘርፍ በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ውስጥ ከኬሚካል እና ነዳጅ ቀጥሎ ሦስተኛው ዋነኛ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ኢንዱስትሪ ነው። ቱሪዝም የውጪ ምንዛሪ ምንጭ በመሆን የበርካታ ሀገራት መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግርና ለውጥ ለማረጋገጥ የሚያስችል ከአገልግሎት ዘርፍ ውስጥ ቅድሚያ ድርሻ የሚወስድ ኢንዱስትሪ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያም ያላትን ይህን ሀብት በማስተዋወቅና በማልማት ከዘርፉ ተጠቃሚ ልትሆን ይገባል።

"ከተማችን አዲስ አበባ የበርካታ ተፈጥራዊ እና ሰው ሰራሽ የቱሪዝም መስህብ ፀጋዎች ባለቤት ነች" የሚሉት አቶ ሃፍታይ፤ ከዚህ ባሻገር ያሏትን እምቅ የቱሪዝም ሃብቶች አልምቶ በከተማዋ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ፋይዳ ሊያመጣ በሚችል መልኩ መጠቀም የሚያስፈልግበት ወቅት ላይ ተደርሷል ነው ያሉት። ይህንንም በመረዳት እንደተቋም የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን በማከናወን ውጤት እየተመዘገበ መሆኑንም ይገልፃሉ። በዚህ መሠረት ባለፉት ሦስት ዓመታት በተከናወነ ተግባር ለአምስት ሺህ 112 የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አዲስ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፣ ለ14 ሺህ760 ተቋማት ደግሞ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እድሳት ማድረግ መቻሉን አመልክተዋል። ይህ ተግባር በቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ከአገልግሎት አሰጣጥ አንፃር የሚስተዋሉ ችግሮች እንዲሻሻሉ የራሱን አስተዋፅዖ እንደነበረው ይናገራሉ።

የሀገር ውስጥ እና የውጪ ጎብኚዎችን ብዛት በቁጥር አስደግፈው የሚናገሩት አቶ ሃፍታይ፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት (2013-2015ዓ.ም) የአገር ውስጥ ጎብኚ ቁጥር 14 ሚሊዮን 484 ሺህ 381 እንደደረሰ ይገልፃሉ። ወደ ከተማዋ የገባው የውጪ አገር ጎብኚ ቁጥርም አንድ ሚሊዮን 085 ሺህ 129 መሆኑን ያነሳሉ።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ከውጪ ቱሪስቶች ወደ ከተማው ኢኮኖሚ 64 ነጥብ 06 ቢሊዮን ብር ፈሰስ ተደርጓል። ለዚህ ስኬት መመዝገብ የከተማው አስተዳደር አዳዲስ የመዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶች ትኩረት መስጠቱ፤ በከተማችን ያለው ሰላም እና የኅብረተሰቡ እንግዳ ተቀባይነት በጉልህ ይጠቀሳሉ።

"ትኩረት ተደርጎ ከተሠሩት ሥራዎች መካከል ለከተማችን ኅብረተሰብ በዘርፉ አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ላይ ነው" የሚሉት ኃላፊው፣ በዚህም ለ34 ሺህ 143 የከተማዋ ሥራ አጥ ወጣቶች በቋሚና በጊዜያዊነት የሥራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ መቻሉን ይገልፃሉ።

አቶ ሃፍታይ እንዳስታወቁት፤ ቱሪዝም በባሕሪው ሰው ተኮር ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በቀጣይም የከተማዋን ሕዝብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፕሮክቶችን በመቀየስና ተግባራዊ በማድረግ፣ የሀገር ውስጥ እና የውጪ ጎብኚን ቁጥር በመጨመርና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱን በማሻሻል አዲስ አበባ ከዘርፉ በሚፈለገው ልክና ደረጃ መጠቀም እንድትችል ትኩረት በመስጠት በጋራ መሥራት ይጠበቃል። በተለይ በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ የቱሪስት መስህቦችና የመዳረሻ ቦታዎችን ዜጎች እንዲጎበኙ ለማድረግ በማስተዋወቁ ረገድ አምባሳደር ሆነው መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የቱሪዝም ዘርፍ በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ውስጥ ከኬሚካል እና ነዳጅ ቀጥሎ ሦስተኛው የዓለማችን ዋነኛ ኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ኢንዱስትሪ ነው። ከዘርፉ ሰው ተኮር ባሕርይ የተነሳ ከ10 ሰዎች ለአንዱ የሥራ እድል በመፍጠር 319 ሚሊዮን የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር ይነገራል። የዓለምን ሰባት በመቶ የውጭ ንግድና 760 ቢሊዮን ዶላር የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ይሸፍናል። በጥቅሉ 10 በመቶ ለሀገራዊ ምርት (GDP) አስተዋፅዖ በማበርከት በተለይም በማደግ ላይ ላሉ ሀገራት የውጭ ንግድ ሚዛን ለማስጠበቅ ከፍተኛ ድርሻ እየተጫወተ ይገኛል።

ይህንን ከከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ድርሻ በማስመልከትና የሚፈጥረውን በጎ ተፅዕኖ በማሰብ በየዓመቱ የዓለም የቱሪዝም ሳምንት ይከበራል። ዘንድሮም በዓለም ለ44ኛ በሀገራችን ደግሞ ለ36ኛ ጊዜ "ቱሪዝም ለአረንጓዴ ልማት። አረንጓዴ ልማት ለቱሪዝም" (Tourism and Green Investment) በሚል መሪ ቃል ከመስከረም --- ጀምሮ እየተከበረ ይገኛል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በመተባበር ለሦስት ተከታታይ ቀናት ይህንን ቀን በልዩ ልዩ ዝግጅቶች አክብሮታል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ባለ ገድሏ ሸዋረገድ ገድሌ



አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ

**ዋለልኝ አየለ**

በታሪክ ውስጥ የአርበኝነት ተጋድሎ ሰፊ ቦታ አለው፤ ምክንያቱም የሀገር ሉዓላዊነት ጉዳይ ነው:: በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ግንባር ቀደም ሆኖ የሚጠቀሰው ደግሞ አፍሪካ ውስጥ ሆና ቅኝ ያልተገዛች ነፃ ሀገር መሆኗ ነው:: ለአውሮፓ አገራት ቢሆን አያስደንቅም ነበር፤ አንዲት አፍሪካዊት አገር የአውሮፓን ቅኝ ገዥ በዱር በገደል ተዋግታ ነፃነቷን ስታስጠብቅ ግን ዓለም አቀፍ ገድል መሆኑ ግልጽ ነው:: እነሆ እነዚህን አርበኞቻችንን ታሪክ ሲያስታውሳቸው ይኖራል::

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ብዙም ባልተነገረውና ባልተዘመረው የሴቶች የአርበኝነት ተጋድሎ ውስጥ ነጥረው የወጡትን አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌን እናስታውሳለን:: ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት ታሪካዊ ክስተቶችን እናስታውስ::

ከ119 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 19 ቀን 1897 ዓ.ም ደራሲ፣ የታሪክ ተመራማሪ፣ የግብርና ሳይንስ ሊቅ፣ የምጣኔ ሀብት ባለሙያና ፖለቲከኛ የነበሩት ብላቴን ጌታ ማኅተመሥላሴ ወልደመስቀል ተወለዱ::

ከ93 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 22 ቀን 1923 ዓ.ም ፒያሳ (አራዳ ጊዮርጊስ) የሚገኘው የዳግማዊ አፄ ምኒልክ መታሰቢያ ሐውልት (ምኒልክ አደባባይ) ተመረቀ:: ይህ የሆነው በንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ የንግሥና በዓል ዋዜማ ነበር:: በዚሁ ዓመት ጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓ.ም አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ሆነው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኑ::

ከ107 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 23 ቀን 1909 ዓ.ም ደራሲ፣ መምህር፣ ባለቅኔ፣ ፀሐፌ ተውኔት፣ ፖለቲከኛ፣ ገጣሚ ... የክብር ዶክተር ከበደ ሚካኤል ተወለዱ::

ከ59 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 23 ቀን 1957 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን (ኢቲቪ) ስርጭቱን ጀመረ:: ይህ ብሔራዊ ቴሌቪዥን በሚቀጥለው ዓመት 60ኛ ዓመቱን እንደሚያከብር በአንዳንድ ፕሮግራሞቹ ተነግሯል::

ከ54 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 24 ቀን 1962 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘው አንጋፋው ሒልተን ሆቴል ሥራው ተጠናቆ በቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ተመረቀ:: የሆቴሉ ዲዛይን የተሠራው በአንድ የአሜሪካ ሥነ ሕንጻ (አርክቴክት) ድርጅት ሲሆን፤ ሆቴሉ ተቀማጭነታቸውን በአዲስ አበባ ያደረጉ ዲፕሎማቶች ቁጥራቸው እየጨመረ መምጣትን ተከትሎ የተገነባ የቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ፕሮጀክት ነው::

ከ134 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 25 ቀን 1882 ዓ.ም የሸዋ ንጉሥ የነበሩት ንጉሥ ምኒልክ ኃይለመለኮት ሣህለ ሥላሴ «ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ» ተብለው ነገሱ::

ከ116 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 25 ቀን 1900 ዓ.ም ፒያሳ የሚገኘው ታሪካዊው የጣይቱ ሆቴል ግንባታው ተጠናቆ ተመረቀ::

በዝርዝር ወደምናየው የአርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ ገድል ስናልፍ፤ ከ74 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 22 ቀን 1942 ዓ.ም የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት በአርበኝነት ተጋድሎ ዘመን የማይሽረው አኩሪ ገድል ከፈፀሙት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዷ የነበሩት ታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ አረፉ::

የዓድዋ ሽንፈቷን ለመበቀል ኢጣሊያ በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን ወረረች:: የኢጣሊያ ወራሪ ኃይልም አንዲትም ቀን እንኳን እፎይ ብሎ ሳይቀመጥ ከአምስት ዓመታት እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ ሌላ የሽንፈት ማቅ ለብሶ ከኢትዮጵያ ምድር ተባረረ:: ታዲያ በዚህ አስገራሚና አኩሪ የመስዋዕትነት ጉዞ ውስጥ ደማቅ የጀግንነት ታሪክ ከፃፉና ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ከተጋደሉ እልፍ የኢትዮጵያ ጀግኖች መካከል አንዷ ታላቋ አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ ነበሩ::

አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ የተወለዱት በ1878 ዓ.ም ደብረ ብርሃን ከተማ ውስጥ ነው:: የቤተ ክህነት ትምህርት ተምረዋል:: ለአቅመ ሔዋን ሲደርሱ ያገቧቸው ባል ብዙም ሳይቆዩ ስለሞቱባቸው ደብረ ሊባኖስ ገዳም ገብተው ተቀምጠው ቆይተዋል::

በ1888 ዓ.ም በጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን ድል የሆነው የኢጣሊያ ጦር ቂሙን ሳይረሳ ሽንፈቱን ሳይዘነጋ ከአርባ ዓመታት በኋላ ዳግመኛ ለብቀላ በተመለሰበት አጋጣሚ በአዲስ አበባ ከተማ በአገር ተቆርቋሪ ዜጎች መሥራችነት «የሀገር ፍቅር ማኅበር» ተቋቋመ። በማኅበሩ በአባልነት ለመጀመሪያ ጊዜ ከተመዘገቡ ሴቶች መካከልም ጀግናዋ ሸዋረገድ ገድሌ አንዷና ግንባር ቀደም ነበሩ።

ወራሪው የኢጣሊያ ጦር ሀገራችን እንደገባ የመጀመሪያ ተግባሩ ያደረገው ለዘመናት በድል ሲውለበለብ የቆየውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በማውረድ የራሱን ባንዲራ መተካትን ነበር።

በወቅቱ ይህን ድርጊት በአይናቸው የተመለከቱት ሸዋረገድ ግን ወራሪውን ጦር ሳይፈሩና ሳይሳቀቁ «ሀገሬ ተወረረች፤ ተዋረደችም» ሲሉ አምርረውና ጮኸው ማልቀሳቸውን ተያያዙት። ሁኔታቸውን ያዩ የጣሊያን ሹማምንትም የእርሳቸውን ድርጊት እንደ ድፍረት በመቁጠር ለክስ አቀረቧቸው። ሸዋረገድ ግን በተለየ ወኔ ተሞልተው «አዎ አልቅሻለሁ! የሀገሬን መወረርና መዋረድ ያወቅሁት የኛ ሰንደቅ ዓላማ ወርዶ የእናንተ ሲወለበለብ በማየቴ ነው:: ሰው ለእናት ሀገሩ ቢያለቅስ ነውሩ የቱ ላይ ነው?!» ሲሉ እልህ በተሞላበት ሁኔታ መለሱላቸው።

ሸዋረገድ ሀገራቸው በጠላት ጦር ዳግመኛ መወረሯ ከታወቀ ወዲህ «ሕይወቴ ሀገሬ ናት» ሲሉ ለመታገል ቆረጡ። ከወራሪው የጠላት ጦር ጋር ሊፋለምና ደሙን ለሀገሩ ሊገብር ለተዘጋጀው ወገን ያላቸውን ሁሉ ሸጠው ትጥቅ እያደራጁና ስንቅ እያዘጋጁ እንዲሁም ከኢትዮጵያውያን ሴቶችም ቁርጥራጭ ጨርቆችን እያሰባሰቡ በጦርነቱ ለሚጎዱ ቁስለኞች እንዲላክ ያደርጉና ይሰጡ ጀመር::

የእሳቸው ድርጊት ግን ለኢጣሊያኖቹ ሰላም አልሰጠም። ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ከመስጠት አልፈው ለክስ እንዲቀርቡ ወሰኑባቸው። ወይዘሮ ሸዋረገድ ለአርበኞች ስንቅ በማቀበላቸው፣ መሣሪያ በመግዛታቸው፣ መረጃ በማሰባሰባቸው፣ መድኃኒት በመላካቸውና ሞራል በመስጠታቸው ምክንያት በተከሰሱ ጊዜም «ለአርበኞች ስንቅ ማቀበሌ እውነት ነው፤ ይህንንም ያደረግኩት ለሀገሬ ክብር ብዬ ነው:: ሰው እንኳን ለሀገሩ... የእናንተ ወይዛዝርት ሀገራቸው ያልሆነችው ኢትዮጵያን ለመውረር የጣታቸውን ቀለበት ሳይቀር መስጠታቸውን ትናገራላችሁ:: እኔም ለሀገሬ የሠራሁት ሲያንሰኝ እንጂ አይበዛብኝም!» በማለት ስለፈፀሙት ድርጊት ሁሉ ኩራት እንደሚሰማቸውና ይህንንም ያደረጉት ለሀገራቸው ክብር ሲሉ እንደሆነ በድፍረት ተናገሩ::

አርበኛ ሸዋረገድ ከሚጠቀሱላቸው ሥራዎቻቸው አንዱ ለቀይ መስቀል ማኅበር ያደርጉት የነበረው ድጋፍ ነው:: በጦርነቱ ዋዜማ፣ በ1927 ዓ.ም ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ንብረታቸውን ሸጠው በማስረከብ ሀገር ወዳድነታቸውን አስከብረዋል:: ከተከሰሱባቸውና «ወንጀል» ተደርገው ከተቆጠሩባቸው ድርጊቶች መካከል አንዱ ይኸው ለቀይ መስቀል ያደርጉት የነበረው ድጋፍ ነው:: እሥር ቤት በገቡ ጊዜም የፋሺስት አስተዳደር ባለሥልጣናት «ቀይ መስቀልንና ሀገር ፍቅር ማኅበርን ትረጂያለሽ» ብለው ክስ አቅርበውባቸው ነበር:: የጠላቶቻቸውን ክስ ከቁብ ያልቆጠሩት አርበኛ ሸዋረገድ ግን «ስለ ነፃነት ከሞቀ ቤታቸው ወጥተው የሌሊት ቁርና የቀን ሐሩር ከሚገርፋቸው የሀገሬ አርበኞች ጎን ተሰልፌ ጠላቴን መውጋቴ ቀርቶ የረሀብና የጥም መድኃኒት እያዘጋጀሁ መላኬ ቁም ነገር ሆኖ ነው የተጠየቅሁበት? እኔ ይህን ባለማድረጌና ለሀገርም ባልቆረቆር፤ እንኳን እነሱ እናንተም እንደምትታዘቡኝ ይሰማኛል» በማለት እጅግ አስደናቂ የሆነ የሀገር ፍቅር የተሞላበትና ቆራጥነት የተቀላቀለበት መልስ ሰጥተዋል።

አርበኛ ሸዋረገድ ከቁሳቁስ እርዳታው ጎን ለጎን ለአርበኞቹ የመረጃ ምንጭም ነበሩ:: በከተማው የሚገኙ የጠላት መረጃዎችን በማሰባሰብና ወደ አርበኞች በምሥጢር በመላክ አርበኞች እንዲጠቀሙባቸው አድርገዋል:: ይህ ተግባራቸውም ከወቅቱ «የውስጥ አርበኞች» መካከል አንዷና ዋነኛዋ ሆነው እንዲቆጠሩ አስችሏቸዋል:: ሸዋረገድ ለኢጣሊያ ሰዎች ወዳጅ በመምሰል ለኢትዮጵያውያን አርበኞች መረጃ ይሰጡ ስለነበር የኢጣሊያ ፋሺስቶች ሸዋረገድ እውነተኛ ወዳጃቸው መስለዋቸው «አርበኞችን ከረዳሽ እኛን አትወጂንም ማለት ነው?» ብለው ሲጠይቋቸው «አዎ አልወዳችሁም! ማነው የሀገሩን ደመኛ የሚወደው?» በማለት ቁርጥ ያለ ምላሽ ሰጥተዋቸዋል::

አርበኛዋ ሸዋረገድ በሚፈፅሟቸው በርካታ ፀረ ፋሺስት እንቅስቃሴዎች ምክንያት ጥርስ የነከሱባቸው የፋሺስት ኢጣሊያ አስተዳደር ባለሥልጣናት ሕይወታቸውን በእስር እንዲገፉና ቆይቶም ሞት እንዲፈረድባቸው ወስነው ነበር። ሆኖም አዚናራ ወደምትባልና በሰሜናዊ ምዕራብ ኢጣሊያ ወደምትገኝ ደሴት ታስረው እንዲቆዩ ከተደረገ በኋላ ፍርዱ ወደ እስራት ብቻ በመቀየሩ ምክንያት የእስር ዘመናቸውን በደሴቲቱ እንዲገፉ ተወሰነባቸው።

ጀግናዋ አርበኛ ሸዋረገድ ግን የቦታ ለውጥና ርቀት አልበገራቸውም። በጠላት ሀገር ሆነውም ጽናታቸው አልተሰበረም፤ ወኔያቸውም አልተሰለበም:: እንዲያውም ወኔያቸውን አጠናክረው ትግላቸውን ቀጠሉ። በእስር ቤቱ የሚቀርብላቸውን ምግብ በአሳሪዎቻቸው ፊት በመድፋትና ጦማቸውን ውለው በማደርም ተቃውሞ ማድረግ ጀመሩ። ከአንድ ዓመት የእስራት ቆይታ በኋላ ከእስራት እንዲለቀቁ በመወሰኑም ወደ አዲስ አበባ የመግባት እድል አገኙ። በወቅቱ ወደ አዲስ አበባ ሲገቡም ሕዝቡ ...

**‹‹ የዘበኛ ሱሪ ካኪና ገምባሌ፣**
**እንኳን ደህና መጣሽ ሸዋረገድ ገድሌ ››**

ብሎ በመግጠም ተቀበላቸው:: በተለይ በጅቡቲ የነበረ አንድ ኢትዮጵያዊ የሰጣቸውን «የይሁዳ አንበሳ» የሚል ጽሑፍና ዓርማ ያለበትን ወረቀት ከንጉሠ ነገሥቱ የተላከ የሚመስል መልዕክት እየፃፉ አርበኞች ተጋድሎ ወደሚያደርጉባቸው ልዩ ልዩ ስፍራዎች በመላክ አርበኞቹ እንዲበረታቱ አድርገውበታል::

አዲስ ዓለም አካባቢ ይገኝ የነበረው የፋሺስት አጣሊያ ምሽግ ኅዳር 5 ቀን 1933 ዓ.ም ሲሰበር ጠቃሚ መረጃዎችን ለአርበኞች በማሰባሰብና በርካታ እቅዶችን በመንደፍ ታላቁን ድርሻ የተወጡት ታላቋ አርበኛ ሸዋረገድ ነበሩ። ምሽጉ ከተሰበረም በኋላ ደጀን መሆኑን ትተው ወደ ውጊያ ለመግባት በመወሰናቸው ከሻለቃ በቀለ ወያ ጦር ጋር ተሰልፈው ጠላትን ተፋልመዋል። በመቀጠልም ወደ ወሊሶ በመሄድ ከደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ጦር ጋር ሆነው ተዋግተዋል። በጦርነቱ የአራት ሰዓታት ውጊያ ላይ ጠላት በጣለው ድንገተኛ አደጋ ከታላቅ ተጋድሎ በኋላ የተማረኩት አርበኛ ሸዋረገድ፣ በድጋሚ በፋሺስት ኢጣሊያ ወታደሮች እጅ በመውደቃቸው የፌጥኝ ታስረው ወደ እስር ቤት ተወረወሩ። የሸዋረገድን ጀግንነት የተመለከተው ሕዝብም ...

**‹‹ የምታስፎክር ሰንጋ ገስሴ፣**
**በጦር መካከል ሳይሆኑ አያሴ፣**
**በጥይት ገዳይ ነጭ ብር ገድሌ፣**
**የሴት ወንድ ናት ሸዋረገድ ገድሌ ››**

ብሎ ጀግንነታቸውን በማድነቅ አወድሷቸዋል:: የጀግኖች አርበኞች ትግል ተጠናክሮ የጠላት ጦር በመጣበት እግሩ በታላቅ ውርደትና በአሳፋሪ ሽንፈት በ1933 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ሲባረር ታላቋ አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌም ነፃ ሆነው ተፈቱ። ከዚህ በኋላ ሕይወትን በነፃነት ማጣጣም ለእኚህ ታላቅ ሴት ትልቅ ትርጉም ነበረው:: ቀድሞ የጀመሩትን አርበኞችን የመርዳት የበጎ አድራጎት ሥራቸውን አጠናክረው ቀጠሉበት። በንግዱ ዘርፍ ተሰማርተውም በርካታ ሰዎችን እንደጠቀሙም ይነገርላቸዋል።

ታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ ታዋቂ ያደረጋቸው የአርበኝነት ሥራቸው ሆነ እንጂ ከመጀመሪያዎቹ የባንክ ተጠቃሚዎች፣ የአክሲዮን ገዥዎች፣ የፋብሪካ ተካፋዮች መካከል አንዷ ነበሩ:: በእነዚህ የንግድ ሥራዎቻቸውም በርካታ ሰዎችን በተለይ ደግሞ ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደቻሉ ታሪካቸው ያስረዳል:: በሃይማኖታቸውም ጠንካራ እንደነበሩ ታሪካቸው የሚናገረው አርበኛዋ፣ የጉለሌ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንንም ያስተከሉት እርሳቸው ናቸው::

ታላቋ አርበኛ ክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ ለወቅቱ አርበኞች በመሣሪያ፣ በስንቅና በመረጃ ያደርጉላቸው ከነበረው ድጋፍ በተጨማሪ ከአንዳንዶቹ ጋር በጦር ሜዳ አብረው ተሰልፈው ተዋግተዋል:: ለአብነት ያህልም ከጀግኖቹ አርበኞች ደጃዝማች በቀለ ወያ እና ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ጋር ተሰልፈው ከጠላት ጦር ጋር ተፋልመዋል:: ለታዋቂው አርበኛ ሌተናል ጀኔራል ጃገማ ኬሎም ልዩ አክብሮት ነበራቸው:: ከዚህ ጋር በተያያዘም ሊጠቀስ የሚገባው አንድ አጋጣሚ አለ::

ንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ከእንግሊዝ ተመልሰው ዙፋናቸው ላይ ቢቀመጡም ጎንደርና ጅማ ከጠላት ጦር አልተለቀቁም ነበር:: «መጀመሪያ የቅርቡን እናስለቅቅ» ተብሎ ወደ ጅማ ሲሄዱ የፋሺስት ጦር የጊቤን ድልድይ ቆርጦ መከላከል ጀመረ:: በዚህ ጊዜ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ጃገማን ያውቋቸው ነበርና ለንጉሠ ነገሥቱ «ለጃገማ ትዕዛዝ ቢሰጡልኝ በአምቦ መንገድ ሄዶ በኋላ በኩል ይቆርጥልኛል» በማለታቸው ጃገማ ከደጃዝማችች ገረሱ ጋር እንዲዘምቱ በደብዳቤ ታዘዙ::

አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ ለንጉሠ ነገሥቱ «ጃንሆይ ይህ ልጅ ገና ሕፃንና የሚያምር ልጅ ነው፤ እንዴት ከሞት ወደ ሞት ይልኩታል? ያሰናብቱት! ጦሩን ቢያዩለትም መልካም ነው» ብለው ስለተናገሩ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ «እውነት ነው፤ ተሣሥተናል፤ እናያለን፤ ጦርህን መጥተን እናያለን ተዘጋጅተህ ጠብቅ፤ ፉከራም ታሰማለህ» ብለው አዘዙ:: ንጉሠ ነገሥቱም የጀግናውን ጦር ጎብኝተው ከጃገማ ጋር ምሳ በሉ:: ከዚያም ጃገማ አዲስ አበባ መጥተው ከንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ሽልማት (25ሺ ብር፣ የወርቅ ሰዓት እና ሙሉ ገበርዲን ሱፍ) ተቀበሉ:: ከዚያም ጃገማ ወደ ደጃዝማች ገረሱ ዘንድ ዘምተውና የለመዱትን ጀብድ ፈፅመው በቦታው የነበረውን የፋሺስት ጦር ዋና አዛዥና ሌሎች መኮንኖችን ማርከው ጦርነቱንም በድል ፈጸሙ::

በመጨረሻም ግሼን ማርያም ሄደው ሥጋ ወደሙን ተቀብለው፤ ከዚያም ወደ ላሊበላ ተጉዘውና ተሳልመው፤ የመጨረሻቸው መሆኑን እየተናገሩ ጥቅምት 22 ቀን 1942 ዓም አረፉ:: የአርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ የመሞታቸው ዜና እንደተሰማ ሕዝቡ እንዲህ ብሎ አንጎራጉሮላቸው ነበር።

**‹‹ እናንት ወጥ ቤቶች በርበሬ ቀንጥሱ፣**
**እናንት ስጋ ቤቶች ሰንጋውን ምረጡ፣**
**ሸዋረገድ ገድሌ ስገና ሲመጡ::**
**ቤተሰቧ ሰፊ ገናና ጥምቀት፣**
**ሸዋረገድ ገድሌ እንደምን ትሙት:: ››**

ታላቋ አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ የአብራካቸው ክፋይ የሆነ ልጅ አላፈሩም:: የልጅ መካን ቢሆኑም የአኩሪ ታሪክ እናት በመሆናቸው ስማቸው በጀግንነት ሕያው ሆኖ እነሆ ሲዘከር ይኖራል::

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ዘናጩ ቴስ- ከአዲስ አበባ እስከ ቬሮና

ቤዛ እሸቱ

እሱ በሥራው ልክ፣ ለሀገሩ ባለው መቆርቆር ልክ በሀገሩ አልታወቀም:: ግን ሙዚቃዎቹን ዘፈን አልሰማም የሚል ሰው እራሱ ያውቃቸዋል:: በተለይ የተወሰኑ ሙዚቃዎቹን አለማወቅ አይችልም:: ያኔ እንዳሁኑ የመገናኛ ብዙኃን ሳይበዙ አንድ ለእናቱ በነበረው የኢትዮጵያ ሬድዮ "ስፖርት" የተሰኘው ዘፈኑ ለበርካታ ዘመናት የስፖርት ፕሮግራም ማድመቂያ በመሆን አገልግሏል:: ይህ ዘፈኑ በበርካታ ትውልዶች ልብና አዕምሮ ውስጥም ቀርቷል:: በርካታ ሥራዎች ቢኖሩትም "ስፖርት"፣ "አዲስ አበባ"፣ "የፍቅር ምግብ"፣ "መጋቢት 28" እና "ውድ ሀገሬ" የተሰኙት ሙዚቃዎቹ በኢትዮጵያውያን የሙዚቃ ወዳጆች ዘንድ ይበልጥ ይታወቃሉ::

ድምፃዊው ተስፋዬ ገብሬ:: እሱ እንደመድረክ መጠሪያ የሚጠቀምበት ቴስ ገብሬ፣ በተለይ የሕይወቱን አብዛኛውን ጊዜ በኖረበትና ዝነኛ በሆነበት ጣሊያን የተከበረ ሥም ነው:: ቴስ ካረፈ 41 ዓመታትን ተቆጥረዋል:: ድምፃዊ ነው፣ ያውም ምን የመሰለ ድምፅ ያለው:: ደግሞም የዜማና ግጥም ደራሲ፤ ጊታር ተጫዋች:: ጣሊያንን መቀመጫው ቢያደርግም ከጣሊያን ተነስቶ በአሜሪካና በተለያዩ ሀገሮች ሥራዎቹን አቅርቧል::

**መጋቢት 28**
**የድላችን ቀን**
**ይከበር ዘላለም**
**በሀገራችን**
**መጋቢት 28**
**በያመቱ ይምጣ**
**የናንተም መሣሪያ**
**ጦር ጋሻችሁ ይውጣ**

እያለ የሚቀጥለው ዘፈኑ በቀድሞ ጊዜ በየዓመቱ መጋቢት 28 በሬዲዮ፣ እንዲሁም በየቦታው ይሰማ የነበረ ዘፈን መሆኑን በርካቶች ያስታውሳሉ:: ነጋዴ ከሆኑት አቶ ገብሬ ምንዳዬና ከእናቱ ወይዘሮ ብዙነሽ ሞላ ለቤቱ የበኩር ልጅ በመሆን ይችን ምድር መኖሪያቸው በነበረው በአዲስ አበባ፣ አራት ኪሎ ተቀላቀለ:: ከመኖሪያቸው ብዙም ሳይርቅ በሚገኘው የሥላሴ ቤተክርስቲያን ውስጥ ይገኝ በነበረ የቄስ ትምህርት ቤት ፊደል ቆጥሯል፤ ዳዊት ደግሟል:: የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በአስፋው ወሰንና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በሽመልስ ሀብቴ ትምህርት ቤቶች ተከታትሏል::

የሰፈሩ የቡሄ ግጥም አውራጅ ነው:: በ12 ዓመቱ በሰፈር ሠርግ ላይ ሲዘፍን የሰሙት የተለየ ድምፅ ባለቤት እንደሆነ መረዳት ችለዋል:: ከዛ ጊዜ ጀምሮ የሰፈር ጓደኞቹም የሱን ፍላጎትና ችሎታ ስለተረዱ ኳስ እንጫወት፣ ባስኬት ቦል እንጫወት ብለው እሱን ማስቸገራቸውን ተዉ:: ከዛን ጊዜ ጀምሮ የሱን ተሰጥዖ ስለተረዱ እነሱ ከኳስ ጋር ሲጫወቱ እሱ ከጉሮሮው ጋር እንዲጫወት መተው ጀመሩ::

ያኔ በስፋት ይንቀሳቀስ በነበረውና አራት ኪሎ በሚገኘው የወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኅበር (ወወክማ) ተሳትፎ ነበረው:: በወወክማ ቆይታው ይዘፍናል፤ ትያትር ይጽፋል፤ ያዘጋጃል፤ ይደርሳል፤ የስፖርት እንቅስቃሴዎች ላይም ተሳታፊ ነበር:: በተለይ በቦክስና በክብደት ማንሳት ውጤታማ ተወዳዳሪ ነበር:: ተስፋዬ ከሲኒማ ቤት የማይጠፋ፤ በፊልሞች ያያቸውን አለባበሶች የሚከተል ዘናጭ ነበር:: ደግሞም ለውጭ ቋንቋዎች ቅርብ ጆሮ ያለው እንግሊዝኛ የሚናገር ቀልጣፋ ነበር:: ጣሊያንኛም መግባቢያው ነበር:: ቋንቋ ይችላልና በወወክማ ቆይታው በእንግሊዘኛም ሆነ በጣሊያንኛ የሚዘፍን ድምፃዊ፤ ብሎም በአማርኛ ግጥምና ዜማ የሚደርስ ድንቅ የጥበብ ሰው ነበር::

ታናሽ እህቱ ወይዘሮ አበራሽ ገብሬ፤ "አባታችን ፍላጎቱ ሁላችንም ዶክተር እንድንሆን ነበር::" ይላሉ:: ሆኖም እናታቸውም ድምፃቸው ማራኪ ነበርና የድምፅ ነገር ከእናቱ የተላለፈለት ሳይሆን እንደማይቀር ይገምታሉ:: በሠፈሩ የቡሄ ጨፋሪ ሕጻናት አለቃ ነበር:: ጥምቀት ያለተስፋዬ አትደምቅም ነበር:: የሠፈሩን ሠርግ እንዲያሞቅ ካለበት ተፈልጎ የሚጠራ ድምፀ መረዋ ነበር::

በወወክማም ሆነ በራሱ ተነሳሽነት የሙዚቃ ችሎታው ዳብሯል:: የሱን ድምፀ መረዋነትና ቅልጥፍና ያዩ "ለምን ክለብ አትሞክርም?" በማለት ላማስኮስ ክለብ ወሰዱት:: በወቅቱ ተደማጭ የነበሩትን የኤልቪስ ፕሪስሊን፣ የፍራንክ ሲናትራንና የሌሎችንም ዓለም አቀፍ ድምፃውያንን ዘፈኖች በግሩም ሁኔታ ይጫወት ነበርና ዝናው ናኘ:: የውጭ





ቋንቋዎች መቻሉ ከሱ ቅልጥፍና ጋር ተደምሮ በመዲናዋ "ተስፋዬ ገብሬ" የሚለው ሥም ታዋቂ ሆኗል:: ይሄን የሱን ዝና የተረዱት የሀገር ፍቅር ማኅበር አመራሮች እነሱ ጋ እንዲጫወት አግባቡት:: እሱም ብዙም ሳያቅማማ የሀገር ፍቅር ማኅበር ድምፃዊ ሆነ::

ተስፋዬ ገብሬ ከድምፅ አወጣጡ አንስቶ አለባበሱ ለምዕራባውያን የሚያደላ ቢሆንም የተቀላቀለው የሀገር ፍቅር ማኅበር ሙሉ በሙሉ የባሕላዊ ዘፈን የሚፈልግ በመሆኑ ብዙም ደስተኛ አልሆነም:: ሆኖም በማኅበሩ ቆይታው አሁን ድረስ የሚሰሙትን "የፍቅር ምግብ" እና "የፍቅር ሰላምታ" የተሰኙ ዘፈኖቹን በዋሽንትና በእጅ ጭብጨባ ብቻ ታጅቦ በግሩም ሁኔታ ሠርቷል:: እሱ የባሕል ዘፋኝ በመሆኑ ብዙም ባይደሰትም የማኅበሩ ዋና ድምፃዊ ሆኖ ነበር:: በመሆኑም ማኅበሩን ለመልቀቅ ጥያቄ ቢያቀርብ እሱን ለመልቀቅ ፍቃደኛ አልሆኑም:: አንድ ዓመት ከስድስት ወር አካባቢ እንደሠራ፤ እንዲያውም ሁሉም ይቅርብኝ በማለት በተግባረ እድ ትምህርቱን መከታተል ጀምሮ ነበር::

ከሀገር ሳይወጣ ከሀገር ፍቅር ማኅበር በተጨማሪ ከመጀመሪያ የራስ ባንድ አባላት ጋር ለተወሰነ ጊዜ ሠርቷል:: የጣሊያኖች ምሽት ክበብ የነበረው ላማስኮስና ጁቬንቱስ ክለብ ሠርቷል:: ከነርሲስ ናልባንዲያን ጋር "ሒሩት አባቷ ማነው?" ለተሰኘው ፊልም ማጀቢያ ሙዚቃ ሠርቷል:: ስደትን የጀመረው የ25 ዓመት ወጣት ሳለ ነው:: ለጉብኝት በሚል ሰበብ የሆዱን በሆዱ ይዞ በባቡር ወደ ጅቡቲ አመራ:: ከጅቡቲ በመርከብ ተሳፍሮ ወደ ጣሊያን ገሰገሰ::

ጣሊያን እንደደረሰ የመጀመሪያ የሙዚቃ ግሩፑ ኦርኬስትራ ዲ አሥመራ ይሰኛል:: አብዛኛው አባላቱ አሥመራ የተወለዱ ጣሊያናውያን ነበሩ:: ከዛ ኦርኬስትራ ስፔታኮሎ የሚሰኝ የቤተሰብ የሙዚቃ ቡድንን ተቀላቅሎ ለሁለት ዓመት ሠርቷል:: ባንዱ በዓመት እስከ 100 ሺዎች የሙዚቃ ሥራዎችን ይሠራ የነበረ በመሆኑ በጣሊያን ዝናው እንዲናኝ በር ከፍቷል:: የባንዱ አመራር የነበረው ካሲዴ በአስደማሚ ድምፁና በዘፈን መሐል በሚናገረው ሃይማኖታዊ ስብከት ተማርኮ መቅጠሩን በጻፈው መጽሐፍ ላይ ገልጿል:: መጨረሻ ላይ ከባለቤቱ ጋር "ብራውን ኤንድ



ዋይት ኤንጅል" የተሰኘ ባንድ አቋቁመዋል::

ቴስ የጃዝ ሙዚቀኛ የሆኑት ሊዊስ አርምስትሮንግ ፍራንክ ሲናትራ ጋር በአንድ መድረክ አብሮ የመሥራት እድል ነበረው:: የእውቁ ድምፃዊ የፍራንክ ሲናትራን መድረኮች ላይ በከፋች ድምፃዊነት ሠርቷል:: በጣሊያን የጃዝ ሙዚቃ ታሪክ ሲነሳ "ቴስ ገብሬ" የሚል ታሪክ አብሮ ይነሳል:: ተስፋዬ በአስር ቋንቋዎች ያዜማል:: ጃዝ ቢሉ ሬጌ፣ ፈንክ ቢሉ ሀገር ቤት ሳለ ሀገርኛውንም ተክኖታል፤ ለረዥም ጊዜ የኖረባትን ጣሊያን ባሕላዊ ሙዚቃዋን የራሱ አድርጎታል:: ጣሊያንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ዓረብኛ፣ ሩሲያኛ፣ ስፓኒሺ፣ እንግሊዝኛና አማርኛ ከሚዘፍንባቸው ቋንቋዎች ጥቂቶቹ ናቸው:: በአንድ ዘፈን ሁለትና ከዛ በላይ ቋንቋዎችን ቀላቅሎ መዝፈንን አውቆበታል:: በአንድ ዘፈኑ ላይ በእንግሊዝኛ፣ በጣሊያንኛ እና በስፓኒሽ አዚሟል::

አብዛኛውን የስደት ዘመኑን የኖረው በጣሊያን ነው:: ሁሉንም የጣሊያን ከተሞች በሥራው አዳርሷል ማለት እስኪቻል ድረስ በርካታ የጣሊያን ከተሞች ተዘዋውሮ ሠርቷል:: በአሜሪካ ኒውዮርክ፣ ላስቬጋስ እና ሎስአንጀለስ ሥራውን ለታዳሚ አቅርቧል:: በአውሮፓ ጀርመን፣ ስዊዲን፣ ስዊዘርላንድ፣ ግሪክ፣ ፈረንሳይ፣ ስፔን እና ክሮሽያ ካዜመባቸው ሀገራት መካከል ይገኛሉ:: በሊባኖስ እና ታይላንድ አስደማሚ ብቃቱን አሳይቷል::

ብዙ መድረክ ቢሠራም፤ በርካታ ሙዚቃዎች ቢጫወትም በርካታ አልበሞችን ግን አልሠራም:: ሁለት የሸክላ አልበምና ሕይወቱ ካለፈ በኋላ በሀገር ውስጥ ለገበያ የቀረበ "ሰላም ለኢትዮጵያ" የተሰኘ አንድ የካሴት አልበም አለው:: በርካታ አልበም ላለማውጣቱ በጣሊያን ያሳተመውን የሸክላ ሲዲ ተከትሎ የመጣበት ቅጣት አንዱ ምክንያት መሆኑን ብዙዎች ይገምታሉ:: በስንት ውጣ ውረድ በጣሊያን ስደት ላይ እያለ ያሳተመው ሸክላ ለገበያ በቀረበ በሦስት ቀናት ሙሉ በሙሉ ከገበያ ተሰብስቧል:: በተጨማሪም በወቅቱ ከያንዳንዱ ሸክላ መክፈል ያለብህን ሳንቲም አልከፈልክምና ያለፈቃድ የጣሊያንን የኮፒ ራይት ሎጎ ተጠቅመኃል በሚል በጣሊያን መንግሥት ለእስር ተዳርጎም ነበር::

ከሦስት ቀናት የገበያ ቆይታ በኋላ ሸክላውም ከገበያ ተሰብስቦ ተወገደ:: ከእስሩና ከገበያ ከመሰብሰቡ በተጨማሪ በወቅቱ ፍርድ ቤት ቀርቦ በወቅቱ ብዙ የነበረውን 2ሺህ 500 ሊሬ እንዲከፍል ተበይኖበታል:: ይህም ከዛ በኋላ አልበም የማሳተም ሞራል እንዲያጣ አንዱ መንስኤ ነው:: ከዛ በኋላ የናይት ክለብ ሥራው ላይ አተኮረ:: ያም ቢሆን በየጊዜው አዳዲስ ሙዚቃዎች መሥራቱን አላቆመም ነበር:: ሆኖም የጣሊያን አድማጭ የሚፈልገው ጣሊያንኛ ቋንቋን ነውና ከሠራቸው ከ100 በላይ ሙዚቃዎች ውስጥ አብዛኞቹ ጣሊያንኛ ነበሩ:: ከሀገሩ ለረዥም ጊዜ ተራርቆ ቢቆይም ሀገሩን ጭራሽ አልረሳም ነበር::

**እናት ኢትዮጵያ**
**ውቢቷ ሀገሬ**
**በጣም ይወድሻል**
**ተስፋዬ ገብሬ......**
**ሰላም ለኢትዮጵያ**
**ውቢቷ ሀገሬ**

**ይኸው ተመለስኩኝ**
**ብዙ ዓለምን ዞሬ።**

እያለ ለሀገሩ ናፍቆቱን ቢገልጽም ወደ ሀገሩ ግን አልተመለሰም:: ሆኖም የአንጀት ካንሰር እንደያዘውና በሽታው የማይድን እንደሆነ ካወቀ በኋላ ከሠራቸው ሙዚቃዎች በተጨማሪ ለሀገር ውስጥ ወገኖቹ የሱ ማስታወሻ የሚሆኑ የአማርኛ ሥራዎችን ቀድቷል:: ከበሽታው ጋር እየታገለ በሽታው ፋታ ሲሰጠው ስቱዲዮ እየገባ ከሠራቸው ሙዚቃዎች ውስጥ 25ቱን በድጋሚ ቀድቷል:: ተስፋዬ በሠራቸው አብዛኞቹ ሙዚቃዎች ላይ የሀገሩን ሥምና ታሪክ እንዲሁም መልክዓ-ምድር አስተዋውቋል:: በዚህም በዓለም አቀፍ ሙዚቃዎች ለዓለም አቀፍ አድማጮች ሀገሩን በጥሩ በማንሳት የሀገሩን ገጽታ ገንብቷል::

ድምፃዊው ሀገሩን ለማስተዋወቅ ካለው ፍላጎት የተነሳ ከሙዚቃው በተጨማሪ ስለሀገሩ በእንግሊዝኛና በጣሊያንኛ መጽሐፍ ጽፎ ነበር:: በአማርኛም የራሱን ታሪክ ጽፎ ነበር:: ከመሞቱ በፊትም ሲሞት መጽሐፎቹ ታትመውና ሙዚቃው ለገበያ ቀርቦ የሚገኘው ገቢ በሀገሩ መብራትና ውሃ ለሌለባቸው አካባቢዎች ለሚኖሩ ወገኖቹ እንዲውሉ ተናዞ ነበር::

ቴስ ግጥም ለመጻፍ እሩቅ ቦታ አይሄድም፤ ከቤተሰቡ ተራርቋልና በናፍቆት እናትና አባቱ ጋ መሄድ ምርጫው ነው:: "ሰላም ለኢትዮጵያ" በሚለው ዘፈኑ፡-

**ሰላም ለአባቴ**
**ታላቁ አቶ ገብሬ . . .**
**እንደምን ሰነበትሽ**
**ብዙነሽ እናቴ**
**ደስታዬ ታላቅ ነው።**

እያለ ቤተሰቡን ያስተዋውቃል:: የፍቅር ሰው ነው፤ አብሮ ጊዜ ያሳለፋቸውን የፍቅር ጓደኞቹን አይረሳም:: ከዛ ውስጥ የመጀመሪያ ልጁ እናት ለነበረችው "ሮማ ናት፣ ሮማ ናት" የተሰኘ ሙዚቃ፤ ሕይወቱ እስኪያልፍ ድረስ ለሦስት ዓመታት ያለመታከት ላስታመመችው የትዳር አጋሩ አንጀሊና፣ እንዲሁም ለልጅነት ፍቅረኞቹ ሁሉ ዘፈን ዘፍኗል:: በዘፈኑ መከፋቱን፣ ምስጋናውንም ሆኖ ናፍቆቱን ገልጾላቸዋል::

ስለተወለደባት፣ ልጅነቱንና ወጣትነቱን በከፊል ስለኖረባት አዲስ አበባ አራት ሙዚቃዎችን ተጫውቶላታል:: የመጀመሪያው ከሀገር ፍቅር ማኅበር ጋር የተጫወተው "አዲስ አበባ" ሲሆን፣ በኢትዮጵያ በካሴት ከወጣው ውስጥ የሚካተተው "አዲስ አበባ ውብ ከተማ" ሳይታተም በጣሊያን የቀረው የኢትዮጵያ ዋና ከተማ እና እዚህ ነው የተወለድኩት የሚሉ ሙዚቃዎችን ለአዲስ አበባ ዘፍኗል:: ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው "ተመለስኩልሽ" ብሎ ያላት ሀገሩን ተመልሶ ሳያያት እ.ኤ.አ. በ1982 እዛው በጣሊያን፣ ቬሮና አረፈ:: በጣሊያን ስሙን በሥራው ተክሏልና ሞቱን መገናኛ ብዙኃን ዘግበውለታል። እንዲሁም፣ በርካታ አድናቂዎቹ ተገኝተው ሥርዓተ ቀብሩ ተከናውኗል::

ድምፃዊው ሁለት ወንድ ልጆች ቢኖሩትም ልጆችን በማሳደግ ረገድ አልታደለም:: የመጀመሪያ ልጁ አያሌው ተስፋዬ እንደተወለደ ድምፃዊው ብዙም ሳይቆይ ወደ ጅቡቲ፣ ቀጥሎም ወደ ጣሊያን ተሰደደ:: በዚህ የተነሳ አባትና ልጅ ከስልክና ከፎቶ የዘለለ ብዙም ሳይገናኙ ኖረዋል:: በጣሊያን ቆይታውም ከጣሊያናዊት ሴት ወንድ ልጅ ቢያገኝም ከልጁ እናት ጋር መስማማት ባለመቻላቸው ልጁን የማሳደግ እድል አልነበረውም:: ጭራሽ በእናትየው ተፅዕኖ የአባትየውን ጥቁርነት መቀበል ተቸግሯል ብሎ በማሰቡ አባትና ልጅ ተቆራርጠው ቀርተዋል::

የሀገራችን የሙዚቃ ባለሙያዎችና ሐያሲያን "ድምፁን እንደፈለገ ማዘዝ የሚችል የተለየ ድምፃዊ" በማለት ይጠሩታል:: በሀገራችን ሀገሩን ያልረሳው ተስፋዬ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ስለታሪኩ ብዙም መረጃ አልነበረም:: አስታዋሽ አያሳጣ ነውና ታላላቅ ወንድሞቼ ሲሰሙት አብሬ እየሰማሁት በማደጌ የሱ አድናቆት ተቀርፆብኛል በሚለው ማርቆስ ተግይበሉ ከቤተሰቦቹ ጋር በመተባበር ከቅርብ ዓመታት በፊት የተስፋዬ የፎቶ ኤግዚቢሽን ተዘጋጅቶ አድናቂዎች የተስፋዬን መልክ እንዲያውቁ አስችሏል:: ከሞተ 41 ዓመታት ቢቆጠርም በያዝነው ዓመት ተስፋዬን ፍለጋ "ከአራት ኪሎ እስከ ቬሮና" የተሰኘ መጽሐፍ ለንባብ በማቅረብ አድናቂዎቹ በቅርበት እንዲያውቁት በር ከፍቷል:: ደራሲው የድምፃዊ ተስፋዬን ታሪክ ፍለጋ ከአዲስ አበባ እስካረፈበት የጣሊያኗ ቬሮና ከተማ በመሄድም ታሪኩን ሰብስቧል::

ዜና

# የአፈር አሲዳማነትን ለመከላከል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጠቁመዋል።

አቶ ሊሬ እንዳስታወቁት፤ አንድ ሄክታር አሲዳማ መሬት ለማከም በአማካይ 30 ኩንታል ኖራ ያስፈልጋል። የአንድ ኩንታል ኖራ ከምርት እስከ አርሶ አደሩ ማሳ እስኪቀርብ ድረስ 955 ብር ወጪ ይጠይቃል።

በበጀት ዓመቱ የታቀደው አሲዳማ መሬት ለማከም ከስምንት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ይጠይቃል ብለዋል።

የመንግሥት ኖራ ማምረቻ ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ኖራ በቂ ባለመሆኑ ከግል ኖራ አምራች ፋብሪካዎች ጋር በጋራ እየተሠራ እንደሆነም ተናግረዋል።

አሲዳማ አፈሩን ለማከም ከኖራ ምርት ዝግጅት እስከ አቅርቦት ሰንሰለቱ ድረስ ያለውን ችግር ለመቅረፍ ከሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ጋር በጥምረት እየተሠራ ይገኛል ያሉት አቶ ሊሬ፤ ጥራቱን የጠበቀ ኖራ በሀገር ውስጥ እንዲመረት ቁጥጥር እየተደረገ መሆኑን አስገንዝበዋል።

በሀገሪቱ ሰባት ሚሊዮን የሚሆን ሄክታር መሬት በአሲዳማነት የተጠቃ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ ሦስት



ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬቱ በከፍተኛ አሲዳማነት የተጠቃ መሆኑን አስታውቀዋል።

በከፍተኛ ሁኔታ በአሲዳማነት ከተጠቃው ሦስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬት እስካሁን ማከም የተቻለው 105 ሺህ ሄክታር መሬት ብቻ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ከኖራ ሕክምናው በተጨማሪ ተፈጥሯዊ ማዳበሪያ በማዘጋጀትና የተለያዩ የሰብል ዓይነቶች በማልማት አሲዳማ መሬት ማከም እንደሚቻል ጠቁመዋል።

በእንክብካቤ ጉድለት እንዲሁም በተፈጥሮ አደጋ የሚከሰት የአፈር ለምነትን ለመከላከል የተፈጥሮ ማዳበሪያ መጠቀም እንደሚገባም አስረድተዋል።

# በአንድ ነጥብ ሦስት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ዘርፎች በአየር ንብረት ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው መንግሥት ለአቪዬሽን፣ ለግብርና እና ለጤና ዘርፎች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል ያሉት አቶ ፈጠነ፤ ኢንስቲትዩቱ አስተማማኝና ቀልጣፋ የአየር ትንበያ አገልግሎት ለመስጠት ከአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ በመመደብ መሠረተ ልማት የተሟላላቸው ሕንፃዎች በመገንባት ላይ ይገኛል ብለዋል።

ማዕከሉ በአፍሪካ የመጀመሪያው ሲሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሦስተኛው መሆኑን ገልጸው፤ የግንባታ ሂደቱም በጥሩ ሁኔታ እየሄደ እና በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚጠበቅ አመልክተዋል፡፡

በሀገሪቱ አውቶማቲክ የአየር ትንበያ ጣቢያዎች እና የምልከታ ሥርዓቶች ተዘርግተዋል ያሉት አቶ ፈጠነ፤ ኢንስቲትዩቱ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመሆን የአየር ትንበያ አገልግሎት አሰጣጥን ለማቀላጠፍና ለማሻሻል የሚረዳ የሰለጠነ የሰው ኃይል ልማት ላይ እየሠራ ይገኛል ነው ያሉት ፡፡

እንደ አቶ ፈጠነ ገለጻ፤ ማዕከሉ የትምህርትና ማሰልጠኛ ክፍሎችን በማካተት በቴክኖሎጂ ዕውቀት ሽግግር ግንባር ቀደም እንዲሆን እየተሠራ ነው፡፡ የሚገነባው ማዕከል በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን አፍሪካ እንዲሁም በዓለም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጣሪ የአየር ትንበያ ማዕከል ይሆናል፡፡

«በተጨማሪም በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የክልል የአየር ትንበያ አገልግሎት ማዕከላትን አቅም እያሳደግን ነው» ሲሉም አክለዋል።

ሕንፃዎቹ በቦሌ ክፍለ ከተማ 18 ሺህ 800 ካሬ ሜትር ስፋት ላይ ያረፉ ሲሆን በአንድ ጊዜ ከአንድ ሺህ 200 በላይ ሰዎችን የማስተናገድ አቅም ያላቸው ናቸው።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ግንባታው ሲካሄድ የቆየው ይህ ፕሮጀክት በኢትዮጵያውያን ሥራ ተቋራጮች እየተካሄደ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል።

# ዓለም አቀፍ

## የቀድሞ የትዊተር የአፍሪካ ሠራተኞች ድርጅቱን ሊከሱ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

ከሥራቸው የተቀነሱ የቀድሞ የትዊተር (ኤክስ) የአፍሪካ ሠራተኞች ድርጅቱን እንደሚከሱ ገለጹ።

ከሥራ ሲቀነሱ ድርጅቱ እንደሚከፍላቸው ቃል የገባውን ገንዘብ ባለመክፈሉ ነው ወደ ክስ ሊያመሩ እንደሚችሉ የተናገሩት።

ያለፈው መስከረም ወር ላይ ኤክስ የአፍሪካ ሠራተኞቹን ከሥራ አስወጥቷል። አብዛኞቹ የወጡት ሠራተኞች በተቋሙ ለወራት ብቻ ነው የሠሩት።

የቀድሞ ሠራተኞቹ ለቢቢሲ «የዓለም ቁጥር አንድ ሃብታም ሰው ገንዘብ ሳይከፍል ሲቀር ያሳዝናል» ብለዋል።

ቢቢሲ ከኤክስ ምላሽ ለማግኘት በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርብም በምላሹ ፈገግ ያለ የምስል መልዕክት ከማግኘቱ በዘለለ ድርጅቱ የተደራጀ መልስ አለመስጠቱ ተገልጿል። በቅርቡ «አሁን ሥራ በዝቶብናል። ኋላ ላይ ሞክሩ» የሚል ምላሽ ኤክስ ለቢቢሲ እንደተሰጠ ታውቋል።

ከዚህ ቀደም ሠራተኞቹን ሙሉ በሙሉ እንደከፈላቸው ድርጅቱ ገልጿል። ኤሎን መስክ አምና ትዊተርን ከገዛ በኋላ በመላው ዓለም ሠራተኞች ተባረዋል። እነዚህም ከ ስድስት ሺህ በላይ ይሆናሉ።

ኤሎን መስክ በቀን አራት ሚሊዮን ዶላር እያጣ እንደሆነ ገልጿል። ኤክስ በጋና፣ አክራ በከፈተው ቢሮ የተቀጠሩት ከ20 ያንሳሉ።

በኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ወቅት ከቤት ሲሠሩ ቆይተው ነው ወደ ቢሮ የተመለሱት።




ኤክስ ከሥራ ካባረራቸው በኋላ የአእምሮ ጤና ቀውስ እንደገጠማቸውና የቤተሰቦቻቸው ገቢ እንደተቋረጠም ለቢቢሲ ገልጸዋል።

ኮንትራታቸው የተቋረጠ ቢሆንም የአንድ ወር ደመወዝ እንደሚሰጣቸው ተነግሯቸው ነበር። ሆኖም ግን ከድርጅቱ የኢሜል ዝርዝር እንዲወጡ ተደርጎ ደሞዛቸውም አልተከፈላቸውም።

ለአንድ ዓመት ያህል ኤክስ ገንዘባቸውን እንዲሰጣቸው ሲከራከሩ እንደቆዩ ይናገራሉ። ለሠራተኞቹ የሕግ ከለላ የሰጠው ሰቨን ሰቨን የተባለ ተቋም ነው።

የተቋሙ ሠራተኛ ክላራ አሎምፒዮ «ነገሩ መሻሻል እያሳየ ነው ብለን ተስፋ ማድረግ ስንጀምር ለሳምንታት ምላሽ ሳይሰጡን ይቆያሉ» ትላለች።

«ከተባረሩ አንድ ዓመት ይሆናቸዋል። ገንዘባቸው አልተሰጣቸውም። ይህ መርህ የጣሰ ነው።» ከሁለት ወር በፊት ሁለቱም ወገኖች ለመነጋገር ተስማምተው ነበር። ሆኖም ግን ኤክስ ቀነ ገደቡን ሳያከብር ቀርቷል።

በ2015 ዓ.ም ሐምሌ ወር ላይ ቢቢሲ በሠራው ዘገባ የኤክስ የቀድሞ የአፍሪካ ሠራተኞች በድርጅቱ ችላ መባላቸውን እንደገለጹ ተነግሯል።

ሠራተኞቹ ያለ ክፍያ፣ የጤና መድኅን፣ የእረፍት ወቅት ክፍያ እንዲሁም የድርሻ ገበያ አማራጮች ነው ከሥራ መባረራቸውን የገለጹት።

የተወሰኑት የተቀጠሩት ከናይጄሪያ ነው። ስለዚህም ቤተሰቦቻቸውን ወደ ጋና ካዘዋወሩ በኋላ ያለ አማራጭ ተቀምጠዋል።

ቢቢሲ ዘገባውን በሠራበት ወቅት ነበር ከኤክስ የሳቅ ኢሞጂ ምላሽ የተሰጠው።

ኤሎን መስክ በዚህ ወቅት በጻፈው ትዊት ለድርጅቱ የመገናኛ ብዙኃን ክፍል የሚላክ ጥያቄ በኢሞጂ ምላሽ እንደሚሰጠው ገልጿል።

ከቢቢሲ ጋር ባደረገው ቆይታ ድርጅቱ አሁን አንድ ሺህ 500 ሠራተኞች እንዳሉት ገልጿል። ቀድሞ ስምንት ሺህ የሚጠጉ ሠራተኞች ነበሩት።

ስለ ሠራተኞች መባረር ቅሬታዎች ሲሰሙ የሦስት ወራት ክፍያ ተሰጥቷቸው እንደወጡ ገልጾ ነበር። ሆኖም ግን የአፍሪካ ቢሮ ሠራተኞች ይህ እንዳልተሰጣቸው ገልጸዋል።

ቢቢሲ ዘገባውን ከሠራ በኋላ ኤክስ ከሠራተኞቹ ጋር መደራደር መጀመሩን ሰቨን ሰቨን አስታውቋል። ሆኖም ግን ምንም ውጤት አልተገኘም።

«አሁን ከዓለም አቀፍ ጠበቆች ጋር እየተነጋገርን ነው። በሌላ ግዛት ትዊተርን እንከሳለን። በስተመጨረሻ ትክክለኛውን ነገር ያደርጉ ይሆናል» ብላለች የሕግ ወኪሏ።

«የውጭ ምንዛሬ ዋጋ ወድቋል። 12 ወራት ሳይከፈላቸው ቆይተዋል። በጣም አሳዛኝ ነው። ኤክስ በመስክ ከተገዛ በኋላ በትንሹ የአፍሪካ ቢሮ ትክክለኛውን ነገር ማድረግ ተስኖታል» ስትልም አክላለች።

ሌሎችም የቀድሞ የኤክስ ሠራተኞች ክስ ከፍተዋል። ተቋሙ 500 ሚሊዮን ዶላር አልከፈለም በሚል በካሊፎርኒያም ክስ ተመሥርቶበታል።

ሲኤንቢሲ እንደዘገበው ከነሐሴ ወዲህ ኤክስ ላይ የተከፈቱ ክሶች በአጠቃላይ ከሁለት ሺህ 200 ይበልጣሉ።




# ልጆች ሀገራችሁን እወቁ!


**እየሩስ ተስፋዬ**

ሰላም ልጆችዬ እንዴት ናችሁ? ሳምንቱ እንዴት አለፈ? ያው እንደ ሁልጊዜው በትምህርት እና በጥናት እንዳሳለፋችሁት ምንም ጥርጥር የለኝም:: ልጆችዬ ስለ ሀገራችሁ ምን ያህል ታውቃላችሁ? መቼም ሀገራችን ኢትዮጵያ ተዝቆ የማያልቅ ጥበብ፣ ታሪክ፣ ባሕል፣ ቅርስ እና ሌሎች መስህቦች እንዳሏት ታውቃላችሁ ወይም ለማወቅ ጥረት ታደርጋላችሁ:: በዚህ በኩልም የቤተሰቦቻችሁ (የአሳዳጊዎቻችሁ) ሚና ከፍተኛ እንደሆነም እተማመናለሁ::

ልጆች ስለ ሀገራቸው ታሪክ፣ ባሕል እና መሰል ነገሮች እውቀት እንዲሁም ግንዛቤ እንዲኖራቸው የቤተሰብ፣ የመምህራን፣ የመንግሥት፣ የእናንተም ድርሻ እና ጥረት ከፍተኛ መሆን ይኖርበታል:: ከነዚህ በተጨማሪ ትምህርት ቤቶችም ተማሪዎቻቸው ታሪካቸውን፣ ሀገራቸውን እና አካባቢያቸውን እንዲያውቁ ለማድረግ ወደ ተለያዩ የጉብኝት ስፍራዎች በመውሰድ ሀገራቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁ ያደርጋሉ:: ልጆችዬ እናንተስ እንዲህ አይነቱ ዕድል ገጥሟችሁ ያውቃል? ‹‹ዕድሉን ገጥሞን ጎብኝተናል›› የሚል ምላሽ እንደምትሰጡኝ ተስፋ አደርጋለሁ:: ከዚህ ቀደምስ ‹ሀገርህን እወቅ› የሚል ክብብ በማቋቋም የተለያዩ ጉብኝቶች ይደረጉ እንደነበር ምን ያህሎቻችሁ ታውቁ ይሆን? ልጆችዬ ካላወቃችሁ ወላጆቻችሁን በመጠየቅ መረዳት ትችላላችሁ ::

ልጆች መገናኛ ብዙኃን እናንተ ስለ ሀገራችሁ እንድታውቁ ለማድረግ በቴሌቪዥን፣ በራዲዮ፣ በመጽሐፍ እና በጋዜጣ መልክ መረጃዎችን በመስጠት ድርሻቸውን እየተወጡ ይገኛሉ:: እኛም በዛሬው ጽሑፋችን የጎብኚዎችን ቀልብ በመሳብ በኩል ተመራጭ ከሆኑት መካከል ጥቂቱን መርጠን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል::


አንድነት ፓርክ


የሰሜን ተራራ

### እንጦጦ ፓርክ

ከባሕር ጠለል በላይ በ3200 ሜትር ላይ የሚገኘው የእንጦጦ ተራራ አዲስ አበባ ከተማ ከተቆረቆረችበት ሥፍራ ነው:: ይህ ታሪካዊ ቦታ አዲስ አበባን ከላይ ወደ ታች ለማየት ምቹ ሲሆን፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በተቀየሰው ‹ሸገርን የማስዋብ ፕሮጀክት› አማካኝነት አይነተኛ የቱሪስት ማዕከል ሆኖ እንዲለማ ተደርጓል:: ቦታውም የእግር ጉዞ ለማድረግ እና ለጎብኚዎች አመቺ እንዲሁም አዝናኝ እንዲሆን ተደርጎ ተሠርቷል:: ለልጆችና ለአዋቂዎች የብስክሌት፣ የፈረስና ሌሎችም የተለያዩ መዝናኛዎችንም ይዟል::

### አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ

አዋሽ ፓርክ ከአዲስ አበባ 215 ኪሎ ሜትር በምሥራቁ የአገራችን ክፍል ይገኛል:: ፓርኩ የተቋቋመው 1958 ዓ.ም ነው:: በውስጡም አጥቢ እንስሳት፣ ከአራት መቶ በላይ የተለያዩ አዕዋፋት፣ ተሳቢ እንስሳት እና ከአራት መቶ በላይ የዕፅዋት ዓይነቶችን ይዟል:: የፓርኩ መለያ ዓርማ የሆነው ሳላ የተባለው የዱር እንስሳ በብዛት የሚኖርበት በመሆኑ ጎብኚዎች ወደ ፓርኩ ያቀናሉ:: በተጨማሪም የአዋሽ ፏፏቴ፣ የተፈጥሮ ፍልውሃ፣ ረዣዥም ሳሮች፣ ከ20 የሚበልጡ የተፈጥሮ መስህቦችን ያየዘ ፓርክ ነው:: የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ በአፋር ክልል አዋሽ ፈንታሌና በኦሮሚያ ክልል ፈንታሌ ወረዳ ውስጥ ይገኛል:: ፓርኩ አምስት መቶ ዘጠና ስኩየር ኪሎ ሜትር ቦታንም ያካልላል::

### የወንጪ ሐይቅ

ይህ ሐይቅ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ በኦሮሚያ ክልል የሚገኝ እጅግ ማራኪ እና ውብ ሐይቅ ነው:: ሐይቁ ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት የሚገኝ ሲሆን፤ በውስጡም ሐይቆችን፣ ፍልውሃዎች እና ሸለቆዎችን አቅፎ የያዘ ነው:: በሐይቁ ደሴት የሚገኘው ጥንታዊ ቤተክርስቲያንም ለአካባቢው ተጨማሪ መስህብ ሆኗል::

### የታላቁ ቤተ መንግሥት አንድነት ፓርክ

የአንድነት ፓርክ በታላቁ ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ውስጥ የተለያዩ ተፈጥሯዊ እና ታሪካዊ መስህቦችን እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ሀገራዊ መገለጫ የሆኑ ሀብቶችን የያዘ ነው:: በውስጡም በጣም ረጅም ዘመናትን ያስቆጠሩ በርካታ ታሪካዊ ሕንፃዎች፣ ከቤተ መንግሥቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቅርሶች፣ የተለያዩ ብሔረሰቦች ባሕል እና እሴት የሚያንፀባርቁ እልፍኞች ተገንብተው የፓርኩ የመዳረሻ አካል እንዲሆን ተደርጓል:: በተጨማሪም ብርቅዬ የዱር እንስሳትን የያዘ የተፈጥሯዊ የእንስሳት መኖሪያ ገጽታ ያለው መካነ እንስሳት (የእንስሳት ቦታ)፤ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ አገር በቀል እጽዋትን የያዘ የእጽዋት ማዕከል እንዲሁም ውብ የአረንጓዴ ሥፍራ የያዘ በመሆኑ ለሀገራችን የቱሪዝም ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል::

### የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ

የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ከባሕር ጠለል 3600 ሜትር በላይ ይገኛል:: በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኘው ይህ ፓርክ፤ በብርቅዬ የዱር አራዊት መስህብ የታደለ ነው:: በሰሜን ተራሮች ከሚገኙ ብርቅዬ እንስሳት መካከል ዋልያ አይቤክስ እና ጭላዳ ዝንጀሮ ተጠቃሽ ናቸው::

ልጆችዬ መቼም ስለ እነዚህ ስፍራዎች ስታውቁ ‹‹ሄደን በጎበኘነው›› ብላችሁ እንደተመኛችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም:: ልጆች ለዛሬው ይህንን ያህል ካልናችሁ ሌሎቹን ደግሞ በሌላ ጊዜ እናስተዋውቃችኋለን:: ለአሁኑ ግን ቤተሰቦቻችሁ የሚችሉ ከሆነም ሙዚየሞችን፣ ፓርኮችን እና የተለያዩ ስፍራዎችን በመጎብኘት የኢትዮጵያን ጥንታዊ ቅርሶችን ከማየት በሻገር ስለ ሀገራችሁ ያላችሁን ግንዛቤ ከፍ እንድታደርጉ ያስችላችኋል::

# ስፖርት





## የአፍሪካ ባሎን ደ ኦር!

**ቦጋለ አበበ**

ታዋቂው የፈረንሳዩ መጽሔት ፍራንስ ፉትቦል በየዓመቱ የዓለም ኮከብ እግር ኳስ ተጫዋቾችን በመምረጥ የባሎን ደ ኦር ሽልማትን ይሰጣል:: ይህ መጽሔት የአፍሪካ ባሎን ደ ኦር ሽልማት ይሸልም እንደነበር ብዙም አይነገርም።

ፍራንስ ፉትቦል ይህንን የዓመቱን የአፍሪካውያን ኮከብ ተጨዋችነት ሽልማት በ1970 ጀምሮት በ1994 አቋርጦታል:: ከዛ በኋላ የየትኛውም አህጉር ተጫዋች በሽልማቱ ውስጥ እንዲካተት አድርጎ ሽልማቱን ቀጥሏል:: ለመሆኑ በፍራንስ ፉትቦል አፍሪካ የመጀመሪያው አፍሪካዊ አሸናፊ ማን ይሆን? በዛሬው የስፖርት ማኅደር ዓምዳችን እንመልከተው።

ሳሊፍ ኬይታ ይባላል:: የዝነኛው የሀገሩ ልጅ ዘፋኝ ሞክሼ ነው:: ማሊያዊ ነው:: የተወለደው በ1946 በመዲናዋ ባማኮ ነው:: የኳስ ሕይወቱን የጀመረው በሪያል ደ ማሊ ሲሆን ሦስት ጊዜ የማሊ ዋንጫን ካነሳ በኋላ ለፈረንሳዩ ሴንት ኤትዬን ፈረመ:: 149 ጨዋታዎች አድርጎ 127 ጎሎችን አስቆጠረ:: አሁን ሊግ 1 እየተባለ የሚጠራውን ዋንጫ ሦስት ጊዜ እንደዚሁም ሁለት ጊዜ የካፕ አሸናፊ ሆኗል:: ከ1962 እስከ 1967 ለአምስት ሲዝኖች በፈረንሳዩ ክለብ ውስጥ ካሳለፈ በኋላ ወደ ኦሎምፒክ ደ ማርሴይ አምርቶ አንድ ሲዝን አሳልፏል:: ሦስት ሲዝን በቫሌንሲያ፣ ሦስት ሲዝን በስፖርቲንግ ፖርቹጋል ካሳለፈ በኋላ ወደ ሰሜን አሜሪካ ሊግ በማምራት በኒው ኢንግላንድ ቲ ሜን ጫማውን ሰቀለ::

ሳሊፍ ኬይታ በሀገሩ ማሊ ዲያራ እና ካኑቴ እስኪመጡ ድረስ እጅግ በጣም የተከበረና ለበርካቶች እንደ ትልቅ አርዓያ የሚቆጠር ነበር:: ገና የ16 ዓመት ታዳጊ ሳለ ነው በ1963 ለማሊ ብ/ቡድን የመጀመሪያ ጨዋታውን ያደረገው:: በ1972 የአፍሪካ ዋንጫ ሁለተኛ


የመጀመሪያው የአፍሪካ ባሎን ደ ኦር አሸናፊ ሳሊፍ ኬታ ከጥቂት ወራት በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፣

ሆነው ሲጨርሱ የእሱ ሚና ላቅ ያለ ነበር::

ጊኒያዊው የፊልም ዳይሬክተር ቼይክ ዱኮሬ በ1994 በእሱ ሕይወት ዙሪያ የሚያጠነጥን "Le Ballon d'or" የተባለ ፊልም ሠርቶለታል:: አሁን የ76 ዓመት አዛውንት የሆነው ሳሊፍ ኬይታ ለሀገሩ ልጆች ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቦቹ አባላትም ጭምር ትልቅ ተምሳሌት ሆኗል:: ለምሳሌ የቀድሞው የባርሴሎና ኮከብ ሴይዱ ኬይታ፣ የቀድሞው የቫሌንሲያ፣ ሊቨርፑል እና ጁቬንቱስ የመሐል አማካይ ሞሐመድ ሲሶኮ እና ለረጅም ዓመት በሬንስ ክለብ አማካይ የነበረው ያያ ኬይታ የወንድሞቹ ልጆች ናቸው::

የዓለማችን ሁሉ ክዋክብት ትልቁ ሕልምና ስኬትም ይሄንኑ ሽልማት ማሸነፍ መሆኑ አያከራክርም። ያም ሆኖ በሽልማቱ ፍትሐዊነት ላይ ዘወትር ምክንያታዊ ጥያቄዎች መነሳታቸው ቀርቶ አያውቅም።

በተለያዩ ዘመናት በርካታ ጥቁር ተጫዋቾች የዓለምን እግር ኳስ አስደምመዋል። ይህን ታላቅ ሽልማት ማሸነፍ የቻለው ብቸኛ ተጫዋች ግን ላይቤሪያዊው ኮከብ ጆርጅ ዊሃ ሆኖ በታሪክ ተቀምጧል። ዊሃ ይህን ሽልማት በማሸነፉ ለበርካታ ጥቁር ከዋክብት ተነሳሽነትን ፈጥሯል፣ የዊሃ ስኬት ለመላው ጥቁር ሕዝብ ዛሬም ድረስ ኩራት ነው። ኮከቡ ግን ሽልማቱን በማሸነፉ ይከፋል እንጂ አይደሰትም። ለዚህም ምክንያት አለው።

በአሁኑ ወቅት ሀገሩ ላይቤሪያን በፕሬዚዳንትነት እየመራ የሚገኘው ዊሃ በ1995 በኤሲ ሚላን ባሳየው አስደናቂ ብቃት ትልቁን ባሎን ደ አር ሽልማት ያሸነፈ የመጀመሪያው ጥቁር ተጫዋች አድርጎታል። ይህን ትልቅ ስኬት ከእሱ በኋላም ለማግኘት የታደለ ጥቁር ኮከብ የለም። ዊሃ በአንድ ወቅት በሰጠው አስተያየት ግን ይህን ሽልማት በማግኘቱ ኩራት እንደማይሰማውና እንደማይደሰትበት አስገራሚ አስተያየት ሰጥቷል።

"የወርቅ ጫማውን በማሸነፌ ኩራት አይሰማኝም፣ ይህ ሽልማት ካገኘሁ በኋላ በአውሮፓ የዘረኝነት ሰለባ ሆኛለሁ" ይላል ዊሃ። የላይቤሪያው ወርቅ የብዙዎችን ልብ በሰበረው ቃለመጠይቁ ሽልማቱን ካሸነፈ በኋላ ሚዲያዎች የዘገቡበትን መንገድ እንዲህ በማለት ያስታውሳል፡- "ሽልማቱን ባሸነፍኩ ማግስት ላ ጋዜጣ ዲሎ ስፖርት በፊት ለፊት ገፁ ጎልቶ በሚታይ ሰፊ ርዕስ ይዞት የወጣው ዘገባ ይታወሰኛል፣ አ ጥቁሩ ሰው የወርቅ ጫማ አሸነፈ" የሚል ነበር።

ዊሃ ሽልማቱን ካሸነፈ በኋላ በሚላን ከተማ ውስጥ ሰዎች በእሱና በአፍሪካ ይስቁ እንደነበር ያስታውሳል። "የወርቅ ጫማውን ሸጠህ ዳቦ ልትገዛላቸው ነው?" ያሉ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በአህጉሩ አፍሪካ ድህነት ይሳለቁ እንደነበርም ይናገራል። ዊሃ ሽልማቱን በማሸነፉ በቆዳ ቀለሙ መጥቆር በደረሰበት ነገር ብቻ አይደለም የሚቆጨው፣ በሽልማቱ ፍትሐዊነት ላይም ምክንያታዊ ጥያቄ ያነሳል። "ድሮግባ ከቼልሲ ጋር ሁሉንም ነገር አሳክቷል፣ ሳሙኤል ኤቶም ከባርሴሎናና ከኢንተር ሚላን ጋር ያላስመዘገበው ክብር የለም፣ ግን የወርቅ ጫማውን ሸለሟቸው? በፍፁም! ምክንያቱም እነሱ ይህን ሽልማት ለአፍሪካውያን ተጫዋቾች የመስጠት ሰብዓዊነቱም የሞራል ልዕልናውም የላቸውም" በማለት ዊሃ አስገራሚ አስተያየቱን ሰንዝሯል።

የዊሃ ታሪካዊ ድንቅ ንግግር ይቀጥላል፡- "ለምርጥ ተጫዋች የሚሰጠው የወርቅ ጫማ አይደለም፣ ትክክለኛው ወርቅ ለአንድ ሰው የሚሰጠው ንጹሕ ልብ ነው፣ ትክክለኛው የወርቅ ሽልማት የሌሎችን ስሜት አለመጉዳት ነው፣ እውነታው ግን እነሱ("ነጮች") ዘረኝነት እንጂ ሰብዓዊነት በውስጣቸው አለመኖሩ ነው"።